ሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል

አገር አቀፍ የአረጋውያን ጥምረት ዓውደ ጥናት

የካቲት 19-20/1990

ግዮን ሆቴል፤አዲስ አበባ

CCPA

ማውጫ

	ገጽ
መግቢያ	1
የዓውደ ጥናቱ የመክፈቻ ንግግር	2
ስለ ኔትወርክ (ቅንጅት) አጠቃላይ መሰረታዊ ሃሳብ	4
ወኪል አካሎች	8
በቅንጅቶች ቅንጅት ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች	10
ህብረትና አጋርነት	11
የቅንጅቶች ታሪክና አመጣጥ በኢትዮጵያ	13
የክርስትያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት ቅንጅት	14
የቅንጅት ተምሳሌት (አካል ጉዳተኞች) ፌዴሬሽን	19
የአረጋውያን ተወካይ ቋሚ አማካሪ ኮሚቴ ስራ ክንውን አጭር መግለጫ	23
የቡድን ስራ	29
1999 ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመት በቅንጅት ስለማክበር	34
የዓውደ ጥናቱ ግምገማ	48
የዓውደ ጥናቱ መዝጊያ	52
የተሳታፊዎች ስም ዝርዝርና አድራሻ	
የዓውደ ጥናቱ ፕሮግራም	

CCRDA

መግቢያ

በዓለም አቀፍ ደረጃ እድገት እያሳየ የመጣው የአረጋውያን ቁጥር የአረጋውያን ጉዳይ ዓለም አቀፍ ትኩረት እንዲያገኝ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በርካታ ዓለም አቀፍ ውሳኔዎች በመተላለፍ ላይ መሆናቸው የዚህ እውነታ ዋና ነጸብራቅ ሆኖ ይታያል፡፡ በአገራችንም ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ የአረጋውያን ጉዳይ በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በተለያየ መልኩ ሲወሳና የአረጋውያንን ህይወት ለማሻሻልም የሚመለከታቸው ሁሉ ተባብረው እንደሚሰሩ በተገኙት መድረኮች ሁሉ ቃል ሲገቡ ተስተውለዋል፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ በተበታተነ መልኩ በየክልላቸውና በየቀበሌያቸው ተወስነው በአረጋውያን ህይወት ዙሪያ የሚሰሩ የተለያዩ ማህበራት፤ መንግስታዊ ያልሆኑ አገር በቀል ድርጅቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡ ነገር ግን ተገናኝቶ በጋራ ጉዳይ ላይ ለመምከር፤ የልምድና የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ በአንድ ማዕከል እንዲገናኙ ማድረግ በተናጠል እያንዳንዱ ማህበርም ሆነ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት እንዲሁም የመንግስት አካል ፍላጎት ሆኖ የቆየውን ዛሬ እውን ለማድረግ የመጀመሪያው እርምጃ ላይ እንገኛለን፡፡

ይህ የእያንዳንዱን አባል ሁለንተናዊ የግል ስብዕና የማይጻረር ነገር ግን በጋራ ዓላማ የሚፈጠር ውህደት ወደመፍጠር ያመራል ተብሎ የሚጠበቀው ዓውደ ጥናት በአይነቱ የመጀመሪያ እንደመሆኑ መጠን ስብጥሩም ሰፊ የሆነበት መድረክ በርካታ ሃሳቦች የሚንሸራሸሩበት ተሳታፊዎች በቅድሚያ የውህደት/ቅንጅትን መሰረታዊ ሃሳብ የሚረዱበትን፤ ጠቀሜታውንና ሊከሰቱ የሚችሉትን ችግሮች ተረድተው ከፊታቸው የሚጠብቃቸውን ችግር የሚመክቱበትን ሁኔታ የሚያመቻቹበትና ቀጣይ እርምጃዎች ምን መሆን እንዳለባቸው የሚወስኑበት መድረክ ነበር፡፡

በመጨረሻ በእግሊዝኛ Networking የምንለው ቃል በዚህ ዓውደ ጥናት ላይ ቅንጅት/ጥምረት/ውህደት በሚሉ አማራጭ ቃላት እንድንጠቀም በተሳታፊዎች መካከል መግባባት ላይ ስለተደረሰ በአውደ ጥናቱ ውስጥ በቀጣይ እነዚህ ቃላት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

CCRDA

<u>የዓውደ ጥናቱ የመክፈቻ ንግግር</u>
<u>በወ/ሮ መዓዛ መድምም</u>
<u>የክልል 14 ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ተወካይ</u>

ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፣

የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች፣

ክቡራትናክቡራን፣

ከሁሉ አስቀድሜ በዚህ ዓውደ ጥናት ላይ ተገኝቼ የመክፈቻ ንግግር እንዳደርግ እድል በማግኘቴ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

አገራችን የብዙ ድንቅ ባህልና ወግ ባለቤት ስትሆን፤ በተለይ ደግሞ አቅመ ደካማና ችግረኛ የሆኑ የአረጋውያንን ችግር በቤተሰብና በዘመድ አዝማድ አማካይነት በማስወገድ ረገድ ረዥም እድሜን ያስቆጠረ አኩሪ ባህላዊ ስርዓት አለን፡፡ ይሁን እንጂ ይህ መልካም የሆነ የመረዳዳት ባህል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከከተሞች መስፋፋትና ከስልጣኔ ጋር በተያያዘ መልኩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰና እየላላ በመምጣቱ በርካታ አረጋውያን የቤተሰብ ድጋፍ በማጣት በአስከፊ የማህበራዊ ኑሮ ችግር ውስጥ ያለ ሟሪና ተንከባካቢ እንዲኖሩ ተገደዋል፡፡

አብዛኞቹ የአገራችን አረጋውያን ከረዥም የዕድሜ ዘመናቸው ውስጥ ብዙውን ለአገርና ለወገን በማገልገል ያሳለፉ እንደመሆናቸው ዛሬ በእርጅና ዘመናቸው በጉልበት መድከምና በገቢ መቀነስ ሳቢያ ለችግር ሲጋለጡ መደገፍ የመንግስትና የህዝብ ሃላፊነት በመሆኑ፤ በዚሁ መሰረት የኢትዮጵያ ፌዴሬላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት የሃገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ልዩ ልዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በቅርቡም የአረጋውያንን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር በመፍታት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሎ የታመነበትና በአገራችን በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነው የማህበራዊ ደህንነት ልማት ፖሊሲ እንዲወጣ ማድረጉ መንግስት ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት የሰጠው መሆኑን ያመለክታል፡፡

የተከበራችሁ እንግዶች !

ዛሬ በአገራችን የሚገኙና ቁጥራቸው ከ3 ሚሊዮን የማያንሱ አረጋውያንን የመንከባከብና የመደገፍ ሃላፊነት በመንግስት አቅም ብቻ ለመወጣት የማይቻል መሆኑን በመገንዘብ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ የአረጋውያን ማህበራትና በይበልጥም ህብረተሰቡ አስፈላጊውን ርብርቦሽ በማድረግ የአረጋውያንን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማምጣት ባለብዙ ፈርጅ እንቅስቃሴ ማካሄድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህ አካላት በተቀናጀ ሁኔታ የአረጋውያንን ጉዳይ እንዲከታተሉና ለችግሮቻቸውም ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት የቀረበ የስራ ግንኙነት መፍጠርና መደጋገፍ ይኖርባቸዋል፡፡

CCRDA

በዛሬው እለት በሚካሄደው በዚህ ዓውደ ጥናት ላይ ከአረጋውያን ጋር የምትሰሩ የልዩ ልዩ ድርጅቶች ተወካዮች እስካሁን በተበታተነና በተሰበጣጠረ ሁኔታ የሚካሄደው እንቃስቃሴ የሚፈለገውን ውጤት እንደማያመጣ ተገንዝባችሁ ቀድሞ የተቋቋመው ብሔራዊ የአረጋውያን ቅንጅት ኮሚቴ የበለጠ ተጠናክሮ ለአረጋውያን ወገኖቻችን ሁሉን አቀፍ አገልግሎት እንዲሰጥ በማስቻሉ በኩል ከፍተኛ አደራና ሃላፊነት የተጣለባችሁ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም በሁለት ቀናት የዓውደ ጥናት ቆይታችሁ ወቅት የአረጋውያን ወገኖቻችንን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር በጥልቀት በመዳሰስ መንግስት ህብረተሰቡና ራሳቸው አረጋውያን በሚያደርጉት የተቀናጀ የሶስትዮሽ ጥረት ችግሮችን መፍታት የሚያስችል ጠንካራ ብሔራዊ የአረጋውያን ቅንጅት መፍጠር የሚያስችሏችሁን ሁኔታዎች እንደምትቀይሱ ያለኝን ጽኑ እምነቴን እየገለጽኩ ይህን ዓውደ ጥናት ላዘጋጀው ለሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል በራሴና በክልል 14 ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

<u>የእንኳን ደህና መጣችሁና የመግቢያ ንግግር</u>
<u>በሚ/ር ጄፍሪ ኦዶኖሂ የሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል ዳይሬክተር</u>

የሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል ዳይሬክተር ሚ/ር ጄፍሪ ኦዶኖሂ ባሰሙት አጭር የመግቢያ ንግግር ተሳታፊዎችን እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኋላ ባለፉት ዓመታት በተከታታይ የተካሄዱት አውደጥናቶችና እስካሁን ሲከበሩ የቆዩት ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ቀኖች ለዚህ ጥምረት መሰረት የጣሉ መሆናቸውን አስታውሰዋል፡፡

ሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል የአረጋውያንን ጉዳይ ብቻውን የሚያካሄድ ሳይሆን እዚህ የተሰበሰቡት ሁሉ ሃላፊነታቸውን በጋራ የሚያካሄዱ መሆን አለባቸው ካሉ በኋላ ዛሬ እዚህ የምትገኙ ተወካዮች ባለፈው ጊዜ የተጀመረውን ጥምረት ወይም ቅንጅት በማዳበር ስለጥምረት መርሆዎችና ተግባሮች አሰራሮችና ናሙናዎች በበቂና በተሻለ ግንዛቤ ለማካሄድ የሚያስችል ሁኔታው የተፈጠረ መሆኑን አሳስበዋል፡፡

በመጨረሻም ሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል ይህንን ጥምረት በማስጀመር በኩል እንደ አዋላጅ እንጂ እንደ ወላጅ ሊታይ የማይገባው መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

CCRDA

ስለ ኔትወርክ (ቅንጅት) አጠቃላይ መሰረታዊ ሃሳብ

(በፓክት ኢትዮጵያ ተወካዮች አቶ ጸጋዬ ቸርነትና ወ/ሮ ሸዋ ጸሃይ በልሁ)

ሁለቱ ከፓክት ኢትዮጵያ በቅንጅት ጉዳይ ላይ ያላቸውን ልምድ ሊያካፍሉ የመጡት ባለሙያዎች በተራ በተራና በመተጋገዝ ስለቅንጅት መሰረታዊ ሃሳቦች ለተሳታፊዎች በሚከተለው መልኩ ጠለቅ ያሉ ማብራሪያዎችና ገለጻዎችን አቅርበዋል፡፡

ትርጉም/ፍቺ

ጥምረት/ቅንጅት/ውህደት ማለት ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ሉአላዊነታቸውን የማይነካና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ቡድን በመፍጠር ለመረጃ ወይም ለማቴርያል ልውውጥ ወይም እቅስቃሴዎችን በጊዜያዊነት ሆነ በዘላቂነት በጋራ ለማከናወን ራሳቸውን የሚያደራጁበት ቅንጅት ወይም ጥምረት ማለት ነው፡፡

ቅንጅት የተለያየ መልክ ሊኖረው ይችላል፡-

- በዘርፍ ላይ ያተኮረ፡ ትምህርት፤ ጤና፤ ጎዳና ተዳዳሪ፤ በአረጋውያን
- በክልል ላይ ያተኮረ
- በአንድ ጉዳይ ላይ ያተኮረ

ሶስትና ከሶስት በላይ የሆኑ ድርጅቶች የጋራ በሆኑ ፍላጎቶች ላይ በመመርኮዝ በጥቅሉ ወይም ተለይቶ ለተቀመጠ የጋራ ግብ ለመድረስ የሚፈጥሩት መደበኛ ወይም ኢመደበኛ ህብረት ማለት ነው፡፡

ስትራቴጂያዊ ቅንጅት ማለት የተለያዩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ያሏቸውን ጥሬ ሃብቶች በማቀናጀት የጋራ የሆኑና በግልጽ የተቀመጡ ህጎችን መርሆ በማድረግ ዋና ዋና ተቃራኒ ሃይሎችን ለመመከት የሚደረግ እንስቃሴን ለማጠናከር የሚፈጠር ጊዜያዊ ህብረት ነው፡፡

ውህደትን ለመፍጠር በሚታሰብበት ጊዜ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸው ነጥቦች፡-

- አባልነት በፈቃደኝነት
- ለብቻቸው ሊሰሩ የማይችሏቸውን እንዲሰሩ
- ቅንጅቶች መደበኛ ወይም ኢመደበኛ ሊሆኑ ይችላሉ
- የእያንዳንዱ አባል የተናጠል ህጋዊ ሰውነት እደተጠበቀ ነው

ተሳታፊዎች ውህደት ለምን ያስፈልጋል ተብለው ተጠይቀው የሚከተሉትን ሃሳቦች ሰንዝረዋል፡-

- አባቶች ድር ቢያብር አንበሳ ያስር እንዳሉት በተናጠል ከመስራት ያለውን ውሱን የገንዘብ አቅም በማቀናጀት የተሻለ ውጤት ይገኛል
- ምሳሌ፡ ክልል 14 ጡረተኞች ማህበር
- ውህደት ሃይል ይፈጥራል፤ ለመተዋወቅ ያስችላል

CCRDA

- ባህልን ስርዓትን ለመለወጥ ይረዳል
- ከተሞክሮ ለመማማር ይረዳል
- በአረጋውያን ጉዳይ ላይ ያለውን የግንዛቤ ችግር አስወግዶ የተሻለ ግንዛቤ ለማስፋፋት
- አንድ ጣት ብቻውን ምንም አይሰራም በአምስት ጣት ከጨበጡ አይለቁም

የትምህርቱ አቅራቢዎች ውህደት የሚያስፈልግበትን ተጨማሪ ነጥቦች እንደሚከተለው አቀረቡ፡

- መረጃ ለመለዋወጥ
- የልዩ ልዩ ግልጋሎቶች ተጠቃሚ ለመሆን
- በተናጠል ከሚደረግ እንቅስቃሴ ይልቅ በህብረት የሚደረገው የተሻለ ውጤት ስላለው
- እውቅናን ለማግኘት
- የተለያዩ እርዳታዎችንና ድጋፎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማግኘት (በአሁኑ ወቅት ለጋሽ ድርጅቶች ድጋፍ ለመስጠት ከሚጠይቁት መስፈርት አንዱ የየትኛው ህብረት አባል ነህ የሚለው ሆኗል)
- ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ወይም ስራዎች ትብብር/ድጋፍ ለማግኘት ይቻል ዘንድ
- በሚቀረጹ ፖሊሲዎች ላይ ወይም ለውጥ በሚያስፈልጋቸው የፖሊሲ ሃሳቦች ላይ ለመሳተፍና የተሸለ ተሰሚነት ለማግኘት


ዘላቂነት ያለው ውህደት/ቅንጅት ለመፍጠር የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች፡-

- በጥናት የተደገፈ መሆን አለበት
- አባላት የጋራ የሆነ ራዕይና ግቦች ሊኖሯቸው ይገባል
- በቅንጅቱ ለመታቀፍ የሚታሰቡ አባላት የጋራ የሆኑ ችግሮችና እንቅፋቶች ሊኖራቸው ይገባል
- የቅንጅቱ አባላት ለጋራ አላማ አስፈላጊውን ጊዜና ገንዘብ ሃይል (ጉልበት) በፈቃደኝነት ለመክፈል ዝግጁ መሆን አለባቸው
- አባላት ስለቅንጅት ጠቀሜታ ትክክለኛ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል
- ሃላፊነትን ወስዶ በቅድሚያ ሁኔታዎችን ለማስተባበር ፈቃደኛ የሚሆን ሰው መኖር አለበት
- አባላት ገንዘባቸውን ለቅንጅቱ እንቅስቃሴ ለማዋል እምነት ሊኖራቸው ይገባል


የጥምረት/የውህደት ዓይነቶች

ልል (Loose) ማንኛውም ሰው ከማንኛውም ሰው ጋር ሊገናኝ የሚችልበት ዓይነት ጥምረት በይበልጥ መረጃ የመለዋወጫ መድረክ ነው፡፡


- በአባላት መካከል የመረጃ ልውውጥ ሊኖር ይችላል (ጋዜጣ)
- የተለያዩ ሃሳቦች መተላለፍና መባዛት
- የአዳዲስ መረጃዎች ተጠቃሚ መሆን
- በአባላቶች መካከል የሚደረግ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ መደጋገፍ



<u>የተማከለ</u> (Centralised)
በአባላት መካከል የሚኖረው ግንኙነት ማዕከላዊ በሆነው አገናኝ አካል አማካኝነት ብቻ



<u>ያልተማከለ</u> (Decentralised)
ከዋናው ማዕከል የሚመነጩ ንኡሳን ማእከሎች ሊኖሩ ይችላሉ (ለምሳሌ ዓለም አቀፍ የሆኑ ጽቤቶች እንደገና በአህጉር ደረጃ ሲዋቀሩ (አፍሪካ፤ ኤሽያ፤ ላቲን አሜሪካ)



ስትራቴጂያዊ ቅንጅቶች

በአንድ የጋራ ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ ዓላማና አቋም ያላቸው ግለሰቦች ወይም ቡድኖች የሚመሰርቱት የጋራ ውህደት ነው፡፡ ለምሳሌ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ፤ የተወሰኑ ቡድኖችን የመብት ጥያቄ በተሻለ ሁኔታ ተሰሚነት እንዲያገኝ የሚመሰረቱና የተነሳሱለት ቅንጅት መልስ/ውሳኔ ሲያገኝ የሚፈርሱ ጥምረቶች ናቸው፡፡

- የቅንጅቱ አባላት ልዩና ጠንካራ የሆነ አላማ (Objective) ይኖራቸዋል
- አላማዎቻቸውም በተጨባጭ እውነታ ላይ የተመረኮዙ ሲሆኑ
- በውጫዊ ርዳታዎች የተደገፉ ሊሆኑ ይችላሉ
- ያልተገደቡና ግልጽ ሆነው የተቀመጡ ዓላማዎች ሊኖሯቸው ይችላል
- አባላቶች የሚመጡ ችግሮችን/አደጋዎችን ለመጋፈጥ ራሳቸውን ዝግጁ ያደርጋሉ
- አባላት ራሳቸውን ለትግሉ ዝግጁ ያደርጋሉ
- የቆመለት ዓላማ ከግቡ ሲደርስ ቅንጅቱ ይፈርስና አባላት ወደቀድሞው ሁኔታቸው ይመለሳሉ
- ነገር ግን በቅንጅቱ የተገኘው ልምድና የዳበረ ግንኙነት አባላት ወደፊትም በቅንጅቱ ለመቀጠል እንዲገፋፉ ያደርጋቸዋል፡፡

ተሳታፊዎች ከዚህ ሃሳብ በመነሳት ለእኛ የሚያስፈልገን ምን ዓይነት ቅንጅት ነው በሚለው ላይ ሃሳብ ሰጡ፡፡

የቅንጅት ደረጃዎች (Stages of Networking)

የቅንጅት ደረጃዎችን በሚመለከት ተሳታፊዎች ያቀረቧቸው ሃሳቦች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

- መረጃ መኖር አለበት
- ችግሩን ማመልከት
- ግልጽ የሆነ ዓላማ

CORDA

- አገናኝ ተቋም ሊኖር ይገባ■ል
- ሃሳብ የሚያመነጩ (Opinion Leaders) መኖር ይገባቸዋል
- ፍላጎት
- ምቹ መድረክ ሊኖር ይገባል
- ገንዘብ
- ለስራ ምቹ የሆነ ሁኔታ
- መተዳደሪያ ደንብ

የተሳታፊዎችን የተለያዩ ሃሳቦች ከተቀበሉ በኋላ ትምህርት አቅራቢዎቹ የቅንጅት አወቃቀር ደረጃዎች ምን ይዘት እንደሚኖራቸው ያቀረቡት (የገለጹት) በዚህ መልክ ነበር፡፡

የቅንጅት አመሰራረት/አወቃቀር ደረጃዎች

- ዝግጅት (Preparation) ፡- ቀስቃሽ ወይም አነሳሽ አባላት የጋራ ፍላጎቶችን ይጠቁማሉ፤ ቅንጅት እንዲፈጠር ሃሳብ ያቀርባሉ፤ ለዚህም ሃይልና ጥሬ ሃይልን ያሰባስባሉ

- ምስረታ (Establishment)፡- አባላት ከመደበኛ እስከ መደበኛ ያልሆኑ ስልቶችንና መዋቅሮችን ያዋቅራሉ፡፡ ቅንጅት ወይም ጥምረት ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ያስተባብራሉ፤ ያዳብራሉ፡፡

- ተግባራዊነት (Operational Stage):- ቅንጅቱ እንቅስቃሴዎችን ይተልማል፤ ጥሬ ሃብትን (ሪሶርስን) ያሰባስባል፡፡ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል እንዲሁም በአባላት መካከል የሚደረግ ትብብርን ያደራጃል፡፡

- የቅንጅት እድገት (Net work Development):- ቅንጅቱ ስትራቴጂያዊ ዕቅዶችን ይነድፋል፡፡ ካካበተው ልምድ በመነሳትም መዋቅራዊና አስተዳደራዊ ለውጦችን ለእንቅስቃሴው አመቺ በሚሆን መልኩ ያደርጋል፡፡

- ዘላቂነት/ቀጣይነት (Sustinability)፡- ቅንጅቱ ለረዥም ጊዜ ህልውናው አስፈላጊ ስለሆኑት የእርዳታ ምንጮች (ገቢ ማስገኛ ዘዴዎች) ይወስናል፡፡

ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች (Support Organisations)

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሆነው በሙሉም ሆነ በከፊል ያላቸውን ጥሬ ሃብት በመጠቀም ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተጠናከረ ወይም ፕሮፌሽናል በሆነ መንገድ ተልእኮአቸውን እንዲወጡ የሚረዱ ድርጅቶች፡፡

ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ደንበኞች እንጂ አባላት የሏቸውም፡፡ ቅንጅቶችም ለአባላቶቻቸው የድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሚያደርጉት አስተዋጽኦ

- የአስተሳሰብ አድማስን በማስፋት በኩል እገዛ ያደርጋሉ
- እውቀትንና ክህሎትን ለማዳበር

CCRDA

- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጥሬ ሃብት የሚያገኙበትን መንገድ በመቀየስ ይረዳሉ
- የቅንጅቶችን ምስረታ ያበረታታሉ እንዲጠናከሩም እገዛ ያደርጋሉ
- ህብረተሰቡን በማስተማር ግንዛቤውን እንዲያዳብር ያደርጋሉ፡፡

ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች፡-

- በትላልቅ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ካሉ የስልጠና ክፍሎች ሊመነጩ ይችላሉ
- አንዳንድ ጊዜ በተወሰነ ጉዳይ ላይ ብቻ ያተኮሩ ይሆናሉ (ኤድስ፤ ጤና አጠባበቅ፤ የጎዳና ተዳዳሪዎች)
- አንዳንድ ጊዜ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ያላቸውን አጠቃላይ ብቃት ለማሳደግ ያለመ (ለምሳሌ ስትራቴጂያው ዕቅድ፤ ቁጥጥርና ግምገማ፤ የገንዘብ አሰባሰብ)
- አልፎ አልፎም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች መሰረት ድጋፍ ይሰጣሉ
- አንዳንዴም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ባልተጠኑና ከዚህ በፊት ባልተዳሰሱ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉበትን መንገድ በቅድሚያ ያመቻቻሉ
- ስለመንግስታዊ ያልሆኑ (ግብረ ሰናይ) ድርጅቶች ሁለንተናዊ መረጃና ልምዶች ቢኖራቸውም እነሱን የመወከል ወይንም ስለነሱ ሆነው የመናገር ስልጣን የላቸውም፡፡

ወኪል አካሎች (Representative Bodies)

- <u>ዘርፋዊ (ሴክቶራል)</u>፤ በእርሻ፤ በጤና፤ ወይም በጎዳና ተዳዳሪ ህጻናት ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ይወክላሉ፡፡

- <u>ክልላዊ (ሪጅናል)</u>፤ በተወሰነ ክልል ያሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ይወክላሉ

- <u>ዘርፋዊና ክልላዊ</u>፤ በተወሰነ ዘርፍ የተሰማሩና በተወሰነ ክልል የሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ይወክላሉ፡፡

ወኪል አካሎች በአባላቶቻቸው ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የተመረጡና አባላቶቻቸውንም በውጪ ግንኙነቶች ለመወከል ሙሉ መብት የተሰጣቸው ናቸው፡፡

ውክልና በሁለት መልኩ ሊታይ ይችላል፡፡

ዘርፋዊ፡ ለሚመለከታቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች
በተለዩ ዘርፎች የመሰማራት ፍላጎት ባላቸው እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች

ክልላዊ፡ ለክልላዊ ባለስልጣናት
በተወሰኑ ክልሎች ለመሰማራት የሚፈልጉ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች

<u>የወኪል አካላት ተግባራት</u>
የመረጃ ልውውጥ፤ ስልጠናና ሌሎች የቅንጅቶችና የድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ተግባራት በተጨማሪ የውክልና ስራዎችንም ያከናውናሉ፡፡

CCRDA

ውክልና፡-

- ዲሞክራሲያዊ ስነምግባር መላበስን ይጠይቃል
- የአባላትን የዓላማ ጽናትና ጥንካሬን (ኮሚትመንት) ይጠይቃል
- የአብላጫ አባላትን ተሳታፊነት ይጠይቃል
- ምናልባትም የአባላት መዋጮ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል (ከውጪ በሚገኙ የገንዘብ እርዳታዎች ሊታገዝ ይችላል)፡፡

<u>ወኪል አካላት ለምን ያስፈልጋሉ?</u>

- ከመንግስታዊ አካላት ወይም እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች የአባል ድርጅቶች አምባሳደር ወይም አፈቀላጤ በመሆን ያገለግላሉ
- አባል ድርጅቶች ከውጭ አካላት ጋር ግንኙነት የሚፈጥሩባቸው አይነተኛ መድረክ በመሆን ያገለግላሉ
- አባል ድርጅቶች የተለያዩ አመለካከቶቻቸውን የሚካፈሉባቸውና የጋራ አቋም የሚይዙባቸው መድረክ በመሆን ሊሰሩ ይችላሉ

<u>አደጋዎች (አስጊ ሁኔታዎች)</u>

- በሌሎች ዘንድ የፖለቲካ ጉዳዮችን የሚያራምዱ አካላት መስለው ሊታዩ ይችላሉ
- ውስጣዊ የስነምግባር ጉድለቶች ሊከሰቱ ይችላሉ
- በአባል ድርጅቶች የተናጠል ግላዊ ጥቅምና ሁሉንም አባላት በሚወክለው አካል ጥቅም መሐከል የሚፈጠር መከፋፈል

በአንድ ጥላ ስር የተሰባሰቡ ድርጅቶች (የቅንጅቶች ቅንጅት) (Apex Bodies)

ትርጉም፡- በአንድ ሃገር ውስጥ የሚገኘውን የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ዘርፍ እንዲወክል በሃገሪቱ ውስጥ ባሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተመረጠ ብሔራዊ አካል ማለት ነው፡፡

ለአባልነት ብቁ የሚሆነው ማነው?
ዲሞክራሲያዊ መዋቅሩ እንዴት ሊዋቀር ይችላል?
ስራውን ለማስኬድ ብዙ ወጪ ይጠይቃል? ወጪውንስ ማን ይሸፍናል?
በሃገሪቱ ውስጥ ያሉት ሁሉም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይታወቃሉን?
በትክክል የግብረ ሰናይ ድርጅቶቹን ፍላጎቶች ያሟላል?/ያረካል?
የመንግስትን ፖሊሲ ይጻረራል?

በአንድ ጥላ ስር የተሰባሰቡ ድርጅቶች (የቅንጅቶች ቅንጅት) (Apex Bodies) ተግባራት ምን ሊሆን ይችላሉ?

- በቅድሚያ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች <u>እርስ በርሳቸው</u>፣ <u>ከመንግስታዊ አካላት</u>፣ <u>ከህዝቡ</u>፣ <u>ከንግዱ ዘርፍ</u>፣ ወይም <u>ከመገናኛ ብዙሃን</u> ጋር የተሻሻለ ግንኙነት እንዲኖራቸው በማድረግ፣
  - ግብረ ሰናይ ድርጅቶቹ የሚመሩበት ህጋዊና ተግባራዊ ደንቦች እንዲኖሩ
  - መልካም ስምና ዝናን በህዝቡ ዘንድ እንዲያገኙ
  - ለሚያካሄዷቸው ስራዎች የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ

CGRDA

፣ የሚገጥሟቸውን አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለመፍታት ብቃት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፡፡

- የግብረ ሰናይ ድርጅቶች የሚመሩበትን የስነ ምግባር ደንብ ያወጣሉ
- ለወጡት የስነ ምግባር ደንቦች ተገዢ እንዲሆኑና ደንቦቹ አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግላቸው
- ያደርጋሉ
- የወጡትን የስነ ምግባር ደንቦችን በማያከበሩ አባል ድርጅቶች ላይ እቀባ ያደርጋሉ
- ግብረ ሰናይ ድርጅቶቹን በተመለከተ ከተለያዩ መንግስታዊ አካላት ጋር ውይይቶችን፤ ድርድሮችን ያድርጋሉ፡፡

በገለጻዎቹ መካከል ትምህርት ሰጪ ከሆኑት ሁለት የፓክት ኢትዮጵያ ተወካዮች አንደኛው በባንግላዴሽ ውስጥ ስለተመሰረተውና በአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ከሚመራው የፖሊሲ አውጪ አካል ውስጥ 2 የግብረ ሰናይ ድርጅቶች ተወካዮች ስለተገኙበት የጥምረቶች ጥምረት ገለጻ አድርገዋል፡፡

በቅንጅቶች ቅንጅት ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

እንቅስቃሴዎቻቸው በውክልና (Representation) ላይና እንዲሁም አባላት የወጡትን የስነ ምግባር ደንቦች ማክበራቸውን መከታተልና በመቆጣጠር ላይ ብቻ ያተኮረ ቢሆን ይመረጣል፡፡

ከነዚህ ውጭ የቅንጅቶች ቅንጅት የሚያከናውኗቸው ስራዎች ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ

ለምሳሌ፡-

የገንዘብ እርዳታዎችን በማከፋፈል ረገድ፣ አንድ በአባላት የተመሰረተ ድርጅት ማን ምን ያህል ገንዘብ ማግኘት እንዳለበት እንዴት ሊወስን ይችላል?

ስልጠናን መስጠት በተመለከተም ይህ በአባላት የተመሰረተ ድርጅት ምን ዓይነት ስልጠናዎች ለምን መሰጠት እንዳለባቸው እንዴት ይወስናል?

ግንኙነቶችን በማስተባበርም ይህ ድርጅት የትኛው ድርጅት ግንኙነቶችን መፍጠር እንዳለበት እንዴት መወሰን ይችላል?

እነኚህ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች የፍላጎቶች ግጭት እንዲፈጠር ሊገፋፉ ይችላሉ፡፡

የተሻለ የሚሆነው ቅንጅቶች ዋና ዋና የስራ ክፍሎችን ማከፋፈል ሲችሉ ነው፡፡ ለምሳሌ

- የገንዘብ እርዳታዎችን ፣ ለለጋሽ ድርጅቶች ቅንጅቶች
- ስልጠናን፣ ለድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች
- ግንኙነቶችን (Contacts)፣ ለሁሉም የቅንጅት ዓይነቶች መስጠት

CCRDA

ህብረትና አጋርነት (Coalitions and Partnerships)

ትርጉም፡-
ህብረት Coalitions፣ የተለያዩ ቡድኖች የሚፈጥሩት ጊዜያዊ የሆነ ጥምረት (ህብረት) ነው፡፡

አጋርነት (Partnerships) በተለያዩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል በቅድሚያ በግልጽ በተቀመጡና ስምምነት ላይ በተደረሰባቸው ትልሞችና ሃላፊነቶች በመመርኮዝ ልማትም ሆነ ጥፋቱ የጋራ በሆነ መልኩ የሚፈጠር እንዲሁም የተወሰኑ ግዴታዎችንም ሆነ ስራዎችን የማጠናቀቅ ሃላፊነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ማለት ነው፡፡

<u>የተለያዩ የአጋርነት (*Partnerships*) ዓይነቶች</u>

- መንግስታዊ ባልሆኑ/ግብረሰናይ ድርጅቶች መካከል ያለ (ቅንጅት፤ ማህበር፤ ፎረም፤ ደንበኞች)
- ግብረሰናይ ድርጅቶችና ማዕከላዊ መንግስት
- ግብረሰናይ ድርጅቶችና በክልል መንግስታት
- ግብረሰናይ ድርጅቶችና ዓለም አቀፍ ኮርፖሬሽኖች
- ግብረሰናይ ድርጅቶችና መገናኛ ብዙሃን
- ግብረሰናይ ድርጅቶች ከለጋሾች ጋር (የሁለትዮሽና የብዙ ድርጅቶች (*Bilateral, Multilateral)*
- ግብረሰናይ ድርጅቶችና ሌሎች የህብረተሰብ ድርጅቶች
  - ሃይማኖታዊ አካላት
  - የሙያ ማህበራት
  - የፖለቲካ ድርጅቶች
  - ሌሎች
    - ዩኒቨርሲቲዎች
    - የምሁራን ማህበራት
    - ህዝባዊ ንቅናቄዎች

መድብለ ብዙ አጋርነት (*Multiple Partnership*) ከላይ የተጠቀሱትን በተለያየ መልኩ በማደባለቅ የሚገኙ፡፡

<u>መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አጋርነት ሊፈጥሩ የሚችሉባቸው ዓላማዎች</u>

- ገንዘብ (መዋዕለ ንዋይ)
- ሌሎች ጥሬ ሃብቶች (በተለይ የሰው ሃይል)
- መረጃና እውቀትን ለማስፋፋት
- ህጋዊነት *Legitimacy*
- ውጤታማ ተሰሚነትን ለማግኘት
- ቅንጅቶችን ከመንግስታዊ ድርጅቶች ባሻገር ለማስፋፋት
- የጋራ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ
- የተሻለ ውጤት ለማስገኘት የጋራ ጥረቶችን ማካሄድ

CCRDA

በአጋርነት መስራት ሊያስከትል የሚችለው ችግር

- የኢኮኖሚ ጥገኝነት ይፈጥራል
- የግል ስልጣንን ማጣት
- በተናጠል ያለንን ተልእኮ እንድንለውጥ ተጽእኖዎች ሊደረጉብን ይችላሉ
- ከተጠቃሚዎቻችን ጋርና ከራሳችን መተዳደሪያ መርሆዎች ጋር ተቃርኖ መፍጠር
- ስምና ዝናን ማጉደፍ
- የማይጨበጡ ተስፋዎችን ማለም
- ድንበርን የጣሰና የጠለቀ ግለሰባዊ ግንኙነት
- በርካታ ቢሮክራስያዊ ውጣ ውረዶች
- ከላይ ወደታች በተዋረድ የሚከናውኑ የስራ ሂደቶች

ሁሉም ጉድኝቶች አጋርነትን አይፈጥሩም
አጋርነት ማለት-

- የጋራ መግባባት ሂደትና ውጤት ነው
- ልማት በሚያስከትለው ለውጥ ላይ የሚደረግ ስምምነት ነው
- የእያንዳንዱን ሃቀኛ የሆነ ጥንካሬና ድክመት በማመዛዘን ላይ የተመሰረ እምነት
- አንደኛው ለሌላኛው የሚሰጠው ህጋዊነት
- ታማኝነት እውነተኛ ያልሆኑ ህልሞችን ማስወገድ

አጋርነት የሚመሰረተው ከመደጋገፍ እንጂ ሙሉ በሙሉ ከጥገኝነት አይደለም።።

CCRDA

የቅንጅቶች ታሪክና አመጣጥ በኢትዮጵያ

(አቶ ሙሉጌታ ባየህ ከክርስትያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት)

ቅንጅት የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የነበረና የሰው ልጆች ባላቸው እንቅስቃሴዎች ማለትም

- የእርስ በርስ ግንኙነት *(Communication)*
- ሰዎች እርስ በርስ የሚስማሙበትን መንገድ በመፍጠር ሁኔታዎች የተሳኩ እንዲሆኑ በማድረግና
- ነገሮችን አብሮ በመስራት (በማከናወን)

ዙሪያ ያተኮሩ ናቸው፡፡
ማንም ሙሉ በሙሉ ራሱን ችሎ ሊቆም አይችልም፡፡ ለመኖር እንድንችልም ራሳችንን የምንረዳበትና ሌሎችን የምናግዝበት ቅንጅት እንፈጥራለን፡፡
ባብዛኛው እንደ እድር፤ ማህበር፤ ደቦ፤ ሃይማኖታዊና የሙያ ማህበራት አንዱና ዋናው መሰረታዊ ይዘታቸው ቅንጅትን መፍጠር ነው፡፡ እነዚህም፡-

- ባጠቃላይ ይዘታቸው
- በአይነታቸው
- በተነሱለት ዓላማ
- በመዋቅራቸው
- በተግባራቸው

የሚገለጹ ይሆናሉ፡፡

ከዚህ በፊት በአገራችን ተፈጥረው የነበሩ ቅንጅቶችንም በሚከተለው መልኩ አብራርተው አቅርበዋል፡፡

<u>የእርዳታ ቅንጅት</u>

በ1984/85 በኢትዮጵያ ለሁለተኛ ጊዜ በተከሰተው ታላቅ ረሃብ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ፤ በመካነ ኢየሱስ፤ በካቶሊካዊት ቤተክርስትያን፤ በሉተራን ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽንና የካቶሊክ እርዳታ አገልግሎት የተመሰረተ አጋርነት ነበር፡፡

<u>የጎዳና ተዳዳሪ ህጻናት ፕሮጀክቶች ቅንጅት</u>

ከ11-12 የሚደርሱ በህጻናት ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች የፈጠሩትና ከአገር ውስጥና ከውጭ ካሉ ድርጅቶች ጋር እንዲሁም በምስራቅ አፍሪካ ካሉ ሌሎች አገሮች ጋር የመረጃ መለዋወጫ መድረክ ነበር፡፡

<u>የህጻናት አድን ቅንጅት</u>

የህጻናት አድን ቅንጅት ደግሞ በህጻናት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥተው የሚንቀሳቀሱ 5 ድርጅቶች ጥምረት ነው፡፡ ቅንጅቱ ሲመሰረት በአባላቱ መካከል ያለውን የመረጃ ልውውጥ ለማቀላጠፍ ነበር፡፡ ባላፉት አመታት ቅንጅቱ በተለይ ህብረተሰቡ ለህጻናት ያለውን አመለካከት ለማስፋትና ለህጻናት ሊደረግ ስለሚገባው ጥበቃ *Advocacy* የጋራ ፕሮግራሞችን አብሮ እስከማራመድ ድረስ እድገት አሳይተዋል፡፡

CCRDA

የክርስትያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት ቅንጅት

ብዙ እድሜ ካስቆጠሩት አቃፊ ቅንጅቶች የክርስትያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት ከአባላት አጠቃላይ ስብሰባዎች ጀምሮ እስከ ቴክኒካዊ የስራ ቡድኖች ድረስ የተለያዩ የቅንጅት መድረኮችን ያስተባብራል፡፡ በክርስትያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት ስር የተዋቀሩትን እነኚህን የተለያዩ የስራ ቡድኖች በተመለከተ ግልጽ የሆነ የተነደፈ የስራ ድርሻ ባይኖርም ሲመሰረቱ በተሰጣቸው መርሃ ግብር መሰረት እስካሁን የሚያራምዱት የጠቅላላ አባላቱን ፍላጎት ነው፡፡ በተጨማሪም በፖሊሲና ስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ የውይይት መድረክ ይፈጥራሉ፡፡

በክርስትያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት አጠቃላይ መርህ ስር የሚንቀሳቀሱት እነዚህ የተለያዩ ቡድኖች ከመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር፤ የተባበሩት መንግስታት ልዩ ልዩ ክፍሎች ጋር፤ ለጋሽ ድርጅቶችና/መንግስታት ከምሁራንና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር የሚኖሩትን ግንኙነቶችና የመረጃ ልውውጥ ይበልጥ ለማጠናከር ይሰራሉ፡፡

የቅንጅቶች ባህሪያት

- በጎ ፈቃደኝነት
- የጋራ መተማመን
- ፈቃደኝነት

የቅንጅት ተግባራት

የቅንጅት ተግባራትን በሚመለከት ምን ዓይነት ሊሆኑ እንደሚገባቸው ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ሃሳቦች ሰንዝረዋል፡፡

- የድጋፍ አገልግሎት እገዛ (በባህል እርሻ ስራ ላይ የሚደረግ መተጋገዝ)
- የመረጃ ልውውጥ
- የሙያ ትምህርት
- መተጋገዝ
- የገንዘብ እርዳታ
- የጋራ የሆነ እሴት መፍጠር
- የጋራ መደጋገፍ *Caring & Sharing*
- ጥብቅና/ድምጽ *Advocacy*
- እውቅና
- እንክብካቤ፣ ቅርስ መንከባከብና ለትውልድ ማስተላለፍ
- በጎ ፍቃደኝነት *Volunteerism*

በቅንጅቶች ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች

- ተሳታፊነትና ሃላፊነት ፡ መስጠትና/ወይም መቀበል
- ማስተባበርና መቆጣጠር
- የአባላትን እንቅስቃሴዎች ቀጥተኛ የሆነ ቁጥጥር ሳያደርጉ ለማስተባበር መቻል
- ግለሰቦችና ተቋማት

CCRDA

- የአባል ግለሰቦች አስተዋጽኦ በተቋማት ሙሉ ድጋፍ ያለው ወይም የታገዘ ሊሆን ይገባዋል፡፡
- መረጃና ተግባር
- ከመረጃ ልውውጥ ምን ማግኘት ይቻላል
- ያመነና ያላመነ (የተለወጠና ያልተለወጠ)
- በቅንጅቱ ሊታቀፉ የታሰቡት እነማን ናቸው (ሁሉም የጋራ ዓላማ አላቸውን?)
- የስራ ሂደትና መዋቅር
- ቅንጅቱ ወደ ተቋምነት እንዲሸጋገር በሚደረገው ግፊት የተነሳ ሊከሰት የሚችለው አዝጋሚነት

ለቅንጅቶች ስኬታማነትን ወይም ውድቀትን የሚያስከትሉ ሁኔታዎች

ግትር ያልሆነ አስተዳደራዊ አሰራር

ግንኙነቶችን የማጠናከር፤ ችሎታዎችን የማዳበርና የጋራ ስራን የማስተባበር ስራዎችን ዓላማ አድርገው የተነሱ ቅንጅቶች የተሻለ ውጤት የሚኖራቸው በማህበራዊ እርስ በርስ ግንኙነቶች ላይ የተመሰረቱ ሲሆኑ ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ማህበራዊ የርስ በርስ ግንኙነቶች ጎልተው የሚታዩት ቅንጅቶቹ ከውስጣቸው በተውጣጡ ሰዎች የሚመሩ ሲሆኑና ግትር ባልሆነና ከጊዜው ጋር ሊራመድ የሚችል አሰራር የሚያራምዱ ሰዎች ሲኖሩት ብቻ ነው፡፡

አንዳንድ የቅንጅት አይነቶች የጋራ ስራዎችን ለማከናወን ሲሉ ሰዎችን ያሰባስባሉ (ለምሳሌ የእርዳታ ስራ የሚሰሩ ቅንጅቶች)፡፡ ሌሎች ደግሞ በተመሳሳይ አላማ የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን በማሰባሰብ እያንዳንዱ ግለሰብ በሚያደርገው እገዛ እንዲጠናከርና የሚገኘውም ውጤት በጣም የጎላ እንዲሆን ያደርጋሉ (ምሳሌ የአካባቢ ጥበቃ ቅንጅት)፡፡

ቅንጅቶች ዘላቂነት እንዲኖራቸው ለማድረግ በጋራ አላማ ላይ የተመሰረተ የተጠናከረ ህብረትን መፍጠርና አባላቶች በጋራ ስራዎች ላይ በአንድነት እንዲሰሩ መፍቀድ ናቸው፡፡

> *ቅንጅቶች ቤተሰባዊ የሆነ ጸባይን እንዲላበሱ መደበኛ ያልሆነ ያሰራር ባህል (Culture of Informality) እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ አለበለዚያ ግን በስራ ላይ ብቻ በማተኮር (too task oriented) በበቂ መልኩ እርስ በርስ ያለመደጋገፍ ወይም ግንኙነት ያለመፍጠር ወይም እንደቤተሰብ አባላት አንዱ አንዱን ያለማገልገል ለመሰሉ ፈተናዎች ይጋለጣሉ፡፡ ቢሆንም ግን ለስራ መትጋትና ፕሮፌሽናላዊ የሆነ አሰራር በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ በተለይም ደግሞ እንደ መንግስታዊ ከሆኑ አካላት ጋር ለሚደረጉ ቅንጅቶች ቤተሰባዊነት ፕሮፌሽናል መዋቅር ከመያዙ ጋር ሚዛናዊ በሆነ መልኩ መራመድ ይኖርበታል፡፡*
>
> (ፊል ድራ)

ይህንን ሃሳብ ማጠናከር ወይም ማጎልበት ማለት ባለቤትነት ለቅንጅት ዘለቄታዊነት ቁልፍ መሆኑን ማንጸባረቅ ነው፡፡ ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ በሁኔታው ውስጥ አስገብተው በሚንቀሳቀሱ አባላት ላይ በግልጽ እንደሚታየው የባለቤትነት ስሜት ለቅንጅቱ እንደው ለመስራት በሚል መንፈስ ብቻ ሳይሆን በትክክለኛው ቅንጅቱ ውስጥ መስራትን የሚያንጸባርቅ ክስተት ነው፡፡ እንዲያው በቀላሉ የቅንጅቱን ስራ መፈጸም

CCRDA

ብቻ ሳይሆን ሃላፊነትንም መስዶ ስራው ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑን በስራ ላይ መዋሉንም ማረጋገጥ ማለት ነው።

ቅንጅቱ በሚፈልገን ሰአትና ቦታ በመገኘት ነባር አባላት በተጠናከረ ሁኔታ እንዲንቀሳቀሱ አዳዲስ አባላትም ወደቅንጅቱ እንዲሳቡ ማድረግ ይኖርብናል። ስራዎችን በግልጽና በጋራ በማከናወን አዳዲስ ውጤቶችንም የማስገኘት ጥረታችንንም መቀጠል ይኖርብናል *(Thai Qualitative Research Network).*

ባለቤትነት የስኬታማ ቅንጅት ውጤትና አስፈላጊም ነው። ለጥሩ እንቅስቃሴ የመገፋፋት ስሜትም መምጣት ያለበት የቅንጅትን ምንነትና ጥቅም በራሳቸው ከሚረዱና ሃላፊነቱንም ለመሸከም ፈቃደኛ ከሆኑ አባላት ነው። ምንም እንኳን ሰዎችና ተቋማት ከቅንጅት ውስጥ የሚገቡበት ምክንያት ተጠቃሚ ለመሆን በሚኖር ፍላጎት ቢሆንም በቅንጅቱ ውስጥ ንቁ የሆነ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚገፋፉት በግልጽም ሆነ በህቡዕ የተተለመ ግቦቻቸው ከሌሎች አባላት ግቦች ጋር ተመሳሳይነት ሲኖራቸውና ቅንጅቱም ለሚያካሄዱት ስራ ተጨማሪ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ሆኖ ሲገኝ ነው።

የቅንጅት አባል ለመሆን ግልጽ የሆነ ምክንያት ሊኖር ይገባል። አላማን በተከተለ መልኩ፤ ወደፊት ለማራመድ፤ ለመቆጣጠር፤ ለማቆየትና ለማስተባበር በሚያስችል መልኩ መዋቅሩን በበቂ ሁኔታ ማስተዋል ያስፈልጋል። የአንድ ቅንጅት ዋና መሰረቶች ማለት እንዲሁ ለመሰብሰብ ብቻ ሳይሆን ተገናኝተው ሃሳቦችን የሚካፈሉ ከዚያም የተለያዩ ተለዋጭ አመለካከቶችንና ስትራቴጂዎችን ይዘው በመመለስ የራሳቸውን ተጽዕኖ በማከል ተግባራዊ ለማድረግ ጽኑ ዓላማ ያላቸው አባላት ናቸው።

<u>በመለያየት (በልዩነት) መማማር</u>

ለቅንጅቶች ስኬታማነት አስፈላጊ ከሆኑት ነጥቦች ሌላው የአባላት ልዩ ልዩ ስብጥር ነው። ልዩነት በርግጥ ሊወገድ የማይችል ነገር ነው። የተለያየ ታሪክና አመሰራረት ያላቸው ሰዎች ይሰባሰቡባቸዋል። በትክክልም ለውጥ የሚገኝባቸው (የማቅለጫ ጋኖች) ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ አይነቱ የልምድ የእውቀትና የፍላጎት ልዩነት በትክክለኛው መንገድ ከተያዙ ልዩነቶች ተመርምረው ለስራ ክፍፍል የሚጣጣሙ በመሆናቸው በርካታ አዳዲስ ትምህርቶችና ሃሳቦች የሚፈልቁባቸው የአዳዲስ ክህሎቶች ልምድ የሚዳብርባቸው አይነተኛ መሳሪያዎች ናቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ ልዩነቶች ለቅንጅት መሰረታዊ የሆኑ ትብብሮችንና ልውውጦችን የሚያዳክሙና ቅራኔን የሚፈጥሩ ሊሆኑ ይችላሉ። በተለይም ባለብዙ የተሰበጣጠረ መሥያና ክልላዊ በሆኑ ቅንጅቶች ውስጥ የቅንጅቶች አመራር ዋናው ሚና አባላቶች ያሏቸውን አሉታዊ ልዩነቶች ገንቢ በሆነ መልኩ ማስታረቅ እንዲችሉ መርዳትና የቅንጅት ባህልን መገንባት ሲሆን ይህም ግቦችን በግልጽ ተንትኖ በማስቀመጥ የአላማ አንድነት ስሜት እንዲፈጠርና የጋራ የሆኑ ጥቅሞች የሚገኙበትን መንገድ በማስረገጥ የሚሰራ ይሆናል።

የቅንጅት ስራዎችን የተወሳሰቡ ከሚያደርጓቸውና ጥሩ ካልሆኑ ውጤቶች መሐል አንዱ የአባላት በየጊዜው መቀያየር ሲሆን አዲስና ጠቃሚ የሆኑ አባላትን ለማፍራት የሚያበቃ ቢመስልም የቅንጅቱን የአሰራር ችሎታ ለማጠንከር የሚደረገውን ጥረት እጅግ አድካሚ ያደርገዋል ስልጠናዎች አንዳንድ ጊዜ መሉ በመሉ አይጠናቀቁም። ምክንያቱም ሰዎች ይቀያየራሉ ሁሌም አዳዲስ ሰዎች ይኖራሉ። ወይም መሰረታዊ ስልጠናውን የወሰዱት ሰዎች አይገኙም። ስለዚህ በቅንጅት አሰራር ስልጠና መቼም አይቆምም (አያበቃም) ማለት ይቻላል። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ሌሎች የቅንጅት

CCRDA

ጥናቶች በአጽንኦት ያሰቀመጡት ውስጣዊ የቁጥጥር ስርዓት ልዩ ዋጋ የሚሰጠው ውጤቱም ደግሞ የማያቋርጥ ተከታታይ የሆነ የራስ መስታወትነት ትምህርታዊ የሚሆነው፡፡

የጋራ ስምምነትን መፍጠር

በተወሰነ አቅጣጫ ማነጣጠርና በግልጽ የተቀመጡ ግቦች ለቅንጅት ስራ ስኬታማነት ተዛማጅ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ቢሆንም ዋናው ቁልፍ ነጥብ ግቦች ጥና ከመጀመራቸው ልክ እንደ ሃሳብ አሰራር ቅደም ተከተል በማያሻማና ግልጽ በሆነ መልኩ የግድ መቀመጥ እንደሌለባቸው ነው፡፡ ይልቁንም በቅድሚያ በበቂ መልኩ ተገልጸው ለመረዳት የሚመቹና ለህብረተሰቡም ስምምነትን የሚያመቻቹ መሆን ሲኖርባቸው አባላትም ደግሞ ግቦቹ በሂደት የሚተገበሩበትን፣ የሚስተካከሉበትንና ቁጥጥር የሚደረግበትን መንገድ በመሉ ልብ የሚያዘረታቱ መሆን አለባቸው፡፡ ያኒ ደግሞ ግቦች ነጻነራቅዊነትን እንዲያስችሉ ለቅንጅቱ ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን የመቀበል ልምድን እንዲያካብቱና የቅንጅቱንም የስራ መርሃ ግብር ቀስ በቀስ ለመረዳት እንዲቻል በራሱ በቅንጅቱም ውስጥ ሆነ በሌሎች ተዛማጅ ክፍሎቹ ውስጥ ይዜንን የሚያመቻች ልዩ የአሰራር ዘዴን ይጠይቃል፡፡

ባላቸው የተለመዱ የተለያዩ ውጤቶችና የአላማ ሂደቶች የተነሳ ግልጽና ባንድ አቅጣጫ የተነጣጠሩ ግቦችን ማንቀሳቀስ ራሱ ለብዙ ቅንጅቶች ውስብስብ ነው፡፡ መተግበር ያለባቸው ስራዎች (ጥናቶች ይካሄዳሉ፣ ስልጠናዎች ይሰጣሉ) እና ማህበራዊ ግንኙነቶች ይዳብራሉ፡፡ ቅንጅት ከእርዳታ ለጪዎች የመነጨ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ የድርጅቱ (ኤጀንሲው) እጀንዳ በራሱ ተጨማሪ አሳሳቢ ጉዳይ ይሆናል፡፡ ከአንድ ቅንጅት የተገኘው ልምድም ሁሉንም ነገሮች ቀድላሉ ለመፈጸም እንደሚያስችል ይጠቁማል፡፡

ለውጥን መምራት (Managing Change)

ለቅንጅቶች ዘላቂነት ወይም ቀጣይነት ቁልፍ ከሆኑት ነገሮች አንዱ ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር በሂደት ለመጣጣም መቻል ነው፡፡ ቅንጅቶች ለበለጠ ጠቀሜታ መስራት የሚችሉት እንደልብ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ሲደረግ እንጂ እንደ ሃውልት ተተክለው ሲቀመጡ አይደለም፡፡ ለጥላ ከለላ ድርጅቶችና መደበኛ በሆኑ ቅንጅቶች ላይ ያለው ትልቅ የጥያቄ ምልክት እዚህ ሊጠቀስ ይገባል፡፡

ስለዚህ ለውጥን የማስተናገድና ተቀብሎ ግንቢ በሆነ መልኩ ማስኬድ መቻል የቅንጅት ጥንካሬ ዋና መለኪያ ነው (መረጋጋት ዋና ጉዳይ በሆነባቸው ተቋሞች በተቃርኖ)

ከንቁ ተሳትፎ ጋር የተቀናጀ በቂና ጥሩ የአመራር ሁኔታ፣ እነስተኛ የስልጣን ተዋረድና ግትር ያልሆነና በጣም ውስን የሆነ ቢሮክራሲያዊ አሰራር ለውጥ የመተበል ችሎታን ከሚያዳብሩበት ሁኔታዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ተቀያያሪ ሁኔታዎችን ለማጣጣምና ለተለያዩ አባላት ሁኔታዎች አመቺ እንዲሆኑ ለማድረግ በፕላን አወጣጥና አፈጻጸም ላይ የሚከሰቱ አሻሚነትንና ተለዋዋጭነትን መገንዘብ የግድ አስፈላጊ ነው፣ አባላትም የየራሳቸውን ሁኔታዎች ከተቋማትና ግለሰብ ሁኔታዎች ጋር በማነጻጸር እንዲደራደሩበት ማድረግ፡፡

ስለቅንጅቶች መጤን ያለባቸው ጉዳዮች

በዚህ ዓውደ ጥናት ሂደት ትኩረት ሊሰጥባቸው ከሚገባቸው ጉዳዮች አንዱ በአረጋያን ጉዳይ ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች የሚፈጥሩት ቅንጅት ሊያደርግ ስለሚችለው

እንቅስቃሴዎች ውይይት ምድረግ ቀጥሎም የቅንጅት ሞዴል መቅረጽና ግቦችና ሊገኙ የሚችሉ ውጤቶችን ግልጽ በሆነ መልኩ ማስቀመጥ መሆን ይኖርባቸዋል።

የቅንጅቶች የተግባር መርህ

- በተቻለ መጠን በህዝብ ዘንድ እንድንታወቅ የሚያደርጉን ነገሮች ቆጠብ ቢሉ (መ.ያ በልብ)
- የተለያዩ አባላት አባል እንዲሆኑ የገፋፏቸው የተለያዩ ምክንያቶችና እንደዚሁም የተለያየ አቅም እንዳላቸው ማወቅ
- ለአመራር ብቁ የሆኑና ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ማሰባሰብ ያስፈልጋል።
- በዚህ ቅንጅት ሊሳተፉ የሚችሉ ሌሎች ተጨማሪ ሰዎች እነማን ናቸው? ሌሎችን ለመጨመር/ለመሳብ መቻል አለብን።
- ሌሎች ሊሰሩ የሚችሉትን ስራ ሳንወስድ ተመሳሳይ ስራ ከሚሰሩት ጋር መቀናጀት ይሻላል *(Avoid Duplication)*

በእለቱ ፕሮግራም ማጠናቀቂያ ላይ የዕለቱ ሶስቱም ትምህርት አቅራቢዎች (አቶ ጸጋዬ ቸርነት፤ ወ/ሮ ሸዋጸሃይ በልሁ እና አቶ መሉጌታ ባየህ በጋራ በመሆን ከተሳታፊዎች ለቀረቡላቸው ልዩ ልዩ ጥያቄዎች መልስ ሰጥተዋል። የተለያዩ የሃሳብ ልውውጦችና ውይይቶችም በተሳታፊዎች መሐል ሰፋ ላለ ጊዜ ከተካሄደ በኋላ የእለቱ ፕሮግራም ተጠናቋል።

CCRDA

ሁለተኛ ቀን የካቲት 20/1990

የቅንጅት ተምሳሌት (*A Model for Networking*)የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን

(በአቶ ይበርታ ታደሰ ከተሃድሶ ጉዳይ መምሪያ)

(የቅንጅት አመሰራረትና ይዘትን በምሳሌ ለማብራራትና ለማሳየት ይረዳ ዘንድ የቀረበ ጽሁፍ)

ይዘት

ሀ. አካል ጉዳትና ጉዳተኝነት
ለ. የአካል ጉዳት ጉዳይ
ሐ. የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት እንቅስቃሴ
መ. የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት ወቅታዊ እንቅስቃሴ
ሰ. የአካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን አመሰራረት
ረ. በአካል ጉዳተኞች የተሐድሶ መስክ የቅንጅታዊ ስራ ተሞክሮ

1. አካል ጉዳትና ጉዳተኝነት

1.1 የአካል ጉዳት

ጊዜያዊ ወይም ዘላቂነት ያለው/ያላቸው በሰዎች አካል አእምሮ ስሜት ላይ የሚደርስ የጤና መቃወስ ወይም ሕመም ወይም በሌላ አባባል በሰው ላይ የሚደርስ ጉዳት ሊባል ይችላል፡፡ በእጅ፣ በእግርና በአይን፣ በጆሮ/በማዳመጫ በአእምሮና በስሜት አካልና ወዘተ ላይ በተለያዩ የተፈጥሮና አደጋ ምክንያቶች የሚከሰቱ ጉዳቶች በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

1.2 የአካል ጉዳተኝነት

ሰዎች በአካላቸው፣ በአምሮአቸውና በስሜት ህዋሳታቸው ላይ በሚከሰተው ጉዳት ምክንያት፣ ማከናወን የሚገባቸውን ተግባራት የማከናወን አቅም ሲያጡ ወይም ለማከናወን ሲሳናቸው የአካል ጉዳተኛ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ (በዓለም ጤና ድርጅት ምደባ መሰረት)

የአካል ጉዳተኝነት በግለሰብ ላይ በሚደርስ ወይም በሚከሰት የአካል፣ የአእምሮ የስሜት ማጣት ወይም ጉድለት የሚገለጽ ሳይሆን ግለሰቡ፣ ህብረተሰቡ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንዳይኖረው በሚገድቡት ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎች ምክንያት የሚፈጠር ችግር ነው (*Disabled Peoples International*)

2. የአካል ጉዳት ጉዳይ *(Disability Issue)*

2.1 የአካል ጉዳት ጉዳይ ለዘመናት ለተቸገረው/ጉዳት ለደረሰበት ሰው ከርህራሄ ወይም ከበጎ አድራጉት ተግባር በመነጨ የሚደረግ የሃይማኖት ተግባር ሆኖ ሲቆጠር ቆይቷል፡፡

ከዚህም የተነሳ ጉዳት የደረሰበት ሰው ምንም ፋይዳ እንደማይሰጥ እየተቆጠረ በሃይማኖት ተቋማት በግል በጎ አድራጊ ድርጅቶች በጎ ፍቃድ በሚመሩ ተቋማት ውስጥ የሰብዓዊ አገልግሎት ተቀባይ ሆነው ሲታዩ ኖረዋል፡፡

2.2 የአካል ጉዳተኞችና ለእነሱ የቆሙ ሐቀኛ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተሟጋች እና ቤተሰቦቻቸው ባደረጉት ያልተቋረጠ ትግል የአካል ጉዳተኝነት ጉዳይ

CCRDA

- የሰብዓዊ መብት
- የእድገት ጥያቄ ሊሆን በቅቷል፡፡

ለዚህም የትግል ውጤት በተባበሩት መንግስታት ቻርተርና የሰላም የሰው ልጆች የሰብዓዊ መብት ነጻነት አጠባበቅ መርሆዎች ላይ መሰረት በማድረግ የወጡት ድንጋጌዎች ማለትም

- *The Universal Declaration of Human Rights*
- *The International Convention of Human Rights*
- *The Declaration on the rights of the mentaly Retarded Person*
- *The declaration on the right of persons with disability*

ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ከዚህም ሌላ ዲሴብልድ ፒፕልስ ኢንተርናሽናልና ሪሃቢሊቴሽን ኢንተርናሽናል የተባሉት ተቋሞች መፈጠርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጠናክሮ መገኘት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

በአጠቃላይ የእነዚህ ድምር ውጤት የአካል ጉዳትና ጉዳተኝነት ጉዳይ የእኩልነትና የእድገት ጥያቄ ሊሆን በመቻሉ አካል ጉዳተኝነት በዜግነታቸው የሙሉ ተሳትፎና የእኩል እድል ተጠቃሚዎች ለመሆን በጉዳታቸው ዓይነት በማህበር በመደራጀትና መብት በችሮታ ሳይሆን በጥረት የሚገኝ የትግል ጥያቄ ጭምር መሆኑን ተረድተዋል፡፡

3. የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማሕበራት እንቅስቃሴ

3.1 የአካል ጉዳትና ጉዳተኝነት ጉዳይ ከምጽዋትና ከችሮታ ተላቆ የሰብዓዊ መብትን የእድገትና ልማት ጥያቄ ሆኖ በመታየቱ በዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች በማህበራት በመደራጀት ለመብታቸው በመታገላቸው ጥያቄያቸውም ሰፊ ተቀባይነት እያገኘ ሊመጣ ችሏል፡፡

3.2 ይኸው ጥያቄና የትግል እንቅቃሴ በመላው ዓለም እየተስፋፋ በመሄዱ የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ እኤአ በውሳኔ ቁጥር 37/52 ያጸድቀውና የአካል ጉዳተኞችን አስመልክቶ ያወጣው የዓለም የድርጊት መርሃ ግብር በአካል ጉዳትና ጉዳተኝነት ላይ ለታየው መሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

3.3 በአገራችን ውስጥ ቀደም ሲል ተቋቁመው የነበሩት፡-

- የኢትዮጵያ ዓይነስውራን ብሔራዊ ማህበር
- የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበርና
- መንግስታዊ ድርጅት የሆነውና የአካል ጉዳትና ጉዳተኞች ጉዳይ በበላይነት የሚከታተለው የቀድሞ የተሐድሶ ድርጅት የዓለም አቀፉ እንቅስቃሴ ተጋሪ እንዲሆን በወቅቱ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡

3.4 ከ1983 ዓ.ም ወዲህ እንቅስቃሴው ከፍተኛ እመርታ በማሳየቱ አካል ጉዳተኞች በጉዳታቸው ዓይነት ከመደራጀት አልፈው በስራ ቡድኖችና በግል ጥረት ጭምር ለመንቀሳቀስ በመቻላቸ ውና ይህም በመንግስት በኩል ድጋፍ በማግኘቱ

- የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማሕበር
- የኢትዮጵያ የስጋ ደዌ ሕመማን ብሔራዊ ማሕበር ሊመሰረቱ በቅተዋል

CCRDA

3.5 የእነዚህ ማህበራት እንቅስቃሴ ቀስ በቀስ በመንግስት፤ በዓለም አቀፍ ድርጅቶችና በሕብረተሰብ ዘንድ ግንዛቤ እያገኘ በመምጣቱ በአሁኑ ወቅት ማህበራቱ በክልል ደረጃ ሊቋቋሙ በቅተዋል፡፡

3.6 ማህበራቱ በመንግስት በኩል ታውቀው ህጋዊ ሰውነት ለማግኘት በመቻላቸው በተለያዩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ የአባላቶቻቸውን ጥቅም በማስጠበቅ በኩል በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ፡፡

4. የአካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን ምስረታ

4. 1 በተናጠል በአካል ጉዳታቸው ዓይነት ሕጋዊ አቋም ኖሯቸው ተደራጅተው የየግላቸውን ጥረት ለዓመታት ሲያደርጉ የቆዩት ብሔራዊ ማህበራት የጋራ ጥያቄያቸውን የሚያስተባብር የሚመራና የሚያቀናጅ ማድረግ መፈጠር ወሳኝና የወቅቱ አገራዊና ዓለም አቀፍ የትግል መሳርያ መሆኑን በመረዳት ከመንግስትና ከበጎ አድራጊ ድርጅቶች ባገኙት ድጋፍና ትብብር ፌዴሬሽናቸውን በጥረታቸው ለመመስረት በቅተዋል፡፡

4.2 የፌዴሬሽኑም አመሰራረት

- በማህበራቱ ፍላጎትና በጎ ፍቃድ ላይ በመመስረት
- እኩል ውክልና ያለው ጊዜያዊ ኮሚቴ (*Steering Committee*) በማዋቀር
- መተዳደሪያ ደንብ በማዘጋጀት
- የመንግስትና የግል በጎ አድራጊ ድርጅቶችን ድጋፍ ለማግኘት ቅድሚያ የግንዛቤ ማዳበር ተግባር በማከናወን
- በአባል ማሕበራት መሀል ስለጋራ መድረክና የቅንጅት ስራ አስፈላጊነት ጠንካራ የቅስቀሳ ተግባር በማከናወን
- የማህበራቱን ብሔራዊ ተሳትፎ ለማስፋት በክልል ደረጃ ማሕበራትን በማቋቋም
- በየክልልና በብሔራዊ ደረጃ አውደ ጥናቶችን በማካሄድ
- በመጨረሻም ከሁሉም ማህበራት ከክልል ጨምሮ በእኩል ውክልና ተሳትፎ የተደረገበት የመስራች ጉባዔ በመጥራት
- እያንዳንዱ አባል ማሕበር የሴት አባላትን ተሳትፎ ያገናዘበ አምስት የምክር ቤት የጉባዔ አባላትን በመወከል

የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን ከብዙ ውጣ ውረድና ድካም በኋላ ሊመሰረት በቅቷል፡፡

4.3 የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን ከተመሰረተ አጭር ጊዜ ቢሆነውም አባል ማሕበራቱን በማስተባበር፤ በማቀናጀት፤ በመምራት በተፈጠረው የጋራ/የቅንጅት መድረክ እያንዳንዱ አባል ማሕበር በሕግ የተቋቋመበትን ዓላማ እንደተጠበቀ ሆኖ

በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የስራ ግንኙነትና የልምድ ልውውጥ መድረክ ለመፍጠር ተችሏል፡፡

ከአሁን ቀደም ያልነበረ በማህበራትና በመንግስት እንዲሁም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች መሐል የጠበቀ አንድነትና ቅንጅት ሊፈጠር ችሏል፡፡

CCRDA

የጋራ ጥያቄ ማንጸባረቂያ መድረክ *(Pressure Group)* ሊሆን ችሏል፡፡

- በአካል ጉዳተኞች በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች መሐል የሶስትዮሽ ቅንጅት መፍጠር ተችሏል፡፡
- በአካል ጉዳትና ጉዳተኝነት ጉዳይ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ግንዛቤ *Public Awareness* ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል፡፡

ማህበራትን በተለያየ ክልሎች ከመቼውም በተሻለ ሁኔታ ለማደራጀት መልካም አጋጣሚ ፈጥሮአል

4.4 በሂደት የገጠሙ ዋና ዋና ችግሮች

- ተሞክሮው በአገራችን አዲስ መሆን/ልምድ ማነስ
- በአባል ማህበራት መሀል የአደረጃጀትና የአቋም ልዩነት (በአመሰራረት አንጋፋና ገና ወጣት የነበሩ ማህበራት መኖር፤ በድርጅታዊ ጥንካሬና ብቃት መለያየትና ወዘተ)
- አባል ማህበራትን ወደ ጋራ ዓላማ ለማምጣት ጊዜ የመውሰድ
- በክልል ደረጃ ሰፊ ተሳትፎ ያላቸው ብሔራዊ ማህበራት ፌዴሬሽኑን ለማዋቀር የገንዘብ አቅም ውሱን መሆንና ይህንንም ለማድረግ ጊዜ መውሰዱ
- መስራች ጉባዔውን ለማካሄድ የገንዘብ ችግር ማዘግየቱ
- ከተመሰረተም በኋላ ቢሆን በተፈለገውና በሚጠበቀው መጠን ለመንቀሳቀስ የበጀት፤ ጽ/ቤት የማግኘትና በቂ የሰለጠነ የሰው ሃይል አለመኖርና ወዘተ ሊጠቀሱ የሚችሉ ችግሮች ናቸው

5.1 በአካል ጉዳተኞች የተሐድሶ መስክ የቅንጅታዊ ስራ ተሞክሮ *

5.1.1 የተለያየ ተልእኮ ነገር ግን የጋራ ዓላማ ያላቸው ማሕበራት የሚያሰተባብራቸው መድረክ/ቅንጅት መፍጠር ከቻሉ አንድ ሊወክላቸው የሚችል የጋራ ጥረታቸውን ሊያቀናጅ የሚችል መድረክ ለመፍጠር እንደሚቻል

5.1.2 የተለያዩ አካላትን የሚያሰባስብ የጋራ ጥረትን የሚያስተባብር መድረክ መፍጠር ከጊዜ፤ ከብዙ ድካምና ካለመሰልቸት የሚደረስበት ሂደት መሆን

5.1.3 የዓላማ አንድነት ፍላጎት ካለ ችግሮችን ተቋቁሞ ከተለሙት ግብ ለመድረስ እንደሚቻልና ከልዩነት አንድነትም እንዳለ

5.1.4 በተናጠል ለመስራት ያልተቻለውን የጋር ጥረትን በማቀናጀት በተሻለ ሁኔታ ለመስራት እንደሚቻል

5.1.5 በተናጠል ያልነበረ ሃይል፤ አንድነት፤ ተሰሚነትና ተቀባይነትን ለመፍጠር እንደተቻለ

5.1.6 በቅንጅት የተሻለና ውጤታማ የሆነ ስራ በቀላሉ ለመስራት እንደሚቻል

5.1.7 ይበልጥ የመተባበር የመደጋገፍና ፈጥኖ ምላሽ የመስጠት እንዲሁም ተባብሮ የመስራት በጎ ፈቃደኝነት መኖር

---

[1] CBR Network (የማህበረሰብ ተሐድሶ ቅንጅት) በእካል ጉዳተኞች የማሕበረሰብ ተሐድሶ መስክ የተሰማሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ወገኖች የተሳተፉበት ነው፡፡

CBRDA

የአረጋውያን ተወካይ ቋሚ አማካሪ ኮሚቴ ስራ ክንውን አጭር መግለጫ (በአቶ ደምሴ አደፍርሰው)

ክብርት ሊቀመንበር
ክቡራትና ክቡራን የጉባዔው አባላት

በአገራችን በኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የአረጋውያንን ደህንነት በተመለከተ በተሃድሶ ጉዳይ መምሪያ በክርስትያን እርዳታና ልማት ድርጅት፤ በሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል እንዲሁም በብርሃን ልጆች በጎ አድራጎት ማህበር፤ በክልል 14 ጡረተኞች ማህበርና በሌሎችም የአረጋውያን መርጃ ድርጅቶች አማካይነት ልዩ ልዩ አውደ ጥናቶች፤ ሲምፖዚየሞች እንዲሁም ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ቀን በአላት በአዲስ አበባና በተለያዩ ቦታዎች ተካሄደዋል። እነዚህ ሁሉ ደህና ውጤት እያመጡ ነው። እነሆ ዛሬም በሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል አማካይነት ይህ የአረጋውያን ጉዳይ አገር አቀፍ ጉባዔ እየተካሄደ ነው። ወደፊትም የአረጋውያን ጉዳይ ስብሰባዎች በአገራችን መካሄዳቸው ይቀጥላል። ይህ ሁሉ የሚያሳየን የአረጋውያን ጉዳይ ከመቼውም በበለጠ በአሁኑ ጊዜ በራሳቸው በአረጋውያን ማህበራትና አረጋውያንን ለመርዳት በተቋቋሙ ድርጅቶች እንደዚሁም በህብረተሰቡና በመንግስት በኩል ከፍተኛ ግንዛቤ እያገኘ መምጣቱንና የአረጋውያንና የቤተሰባቸውን ኑሮ ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት በጥሩ መንገድ ላይ መሆኑ ነው።

በተለይ ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት ህዳር 17-19/1989 በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማሰልጠኛ ማዕከል አዳራሽ በተሓድሶ ጉዳይ መምሪያ አማካይነት በተካሄደው አገር አቀፍ ዓውደ ጥናት ላይ "ለአረጋውያን ስለሚሰጥ እንክብካቤና ድጋፍ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ከፍተኛ ስብሰባ በተደረገ ጊዜ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤት ተወካዮች፤ የአረጋውያን ማህበራት ተወካዮች፤ ልዩ ልዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ረጂ ድርጅቶችና ከየክልሉ የመጡ የመንግስት መ/ቤቶችና የህብረተሰብ ተወካዮች በጠቅላላ 64 የጉባዔ አባላት ተገኝተዋል። በዚህ ጉባዔ ላይ አረጋውያንን በተመለከተ ብዙ ጉዳዮች ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን የአረጋውያንን ደህንነትና እንክብካቤ የሚመለከቱ ዝርዝራቸው ከዚህ መግለጫ ጋር የተያያዘ ባለ 12 ነጥብ የስራ ፕላን ያወጣ ሲሆን እነዚህን የስራ ፕላኖችና ሌሎችንም የአረጋውያንን ጉዳዮች ከተሃድሶ ጉዳይ መምሪያ ጋር እየተመካከረ የሚከታተል አንድ <u>የአረጋውያን ተወካይ ቋሚ አማካሪ ኮሚቴ</u> በጉባዔው ከተገኙ ድርጅቶችና ማህበራት ተወካዮች መካከል በተሃድሶ መምርያ አማካኝነት ተውጣጥተው እንዲመደቡ በጉባዔው በተወሰነው መሰረት ይህ ኮሚቴ በተሃድሶ ድርጅት ስር ተቋቁሞና ሰብሳቢው ጸሃፊ ከተሃድሶ ድርጅት ሆነው ኮሚቴው ከታህሳስ 9/1989 ጀምሮ እስከ መስከረም 29/1990 ድረስ ከ18 ያላነሱ ስብሰባዎችን በማድረግ ከተሃድሶ መምሪያ ጋር በቅርበት በመሰከር ሰርቷል።

የዚህ የአረጋውያን ተወካይ አማካሪ ኮሚቴ አባላት

1. አቶ አበራ ገ/ስላሴና አቶ አሰፋ ባልሄር ከተሃድሶ መምሪያ	ሰብሳቢ
2. አቶ ሃይለማርያም ከበደ አቶ ለገሰ ረታ	ጸሐፊ
3. አቶ ፋኖሴ ተ/ስላሴ ከጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር	አባል
4. አቶ አሸናፊ ደስታ ከክልል 14 ጡረተኞች ማህበር	አባል
5. አቶ ደምሴ አደፍርሰውከማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ጡረተኞች	አባል
6. መቶ አለቃ ጌታሁን አበራ ወረዳ 11 ጡረተኞች ራስ አገዝ ህ/ስ/ማ	አባል

CCRDA

7. ወ/ሮ ፍሬይወት ገብረህይወት በሙሉ በተቀነባበረ የከተማ ልማት ፕ. አባል
8. ሚስ ሳራ ሀርበርት ጆንስ ዶ/ር ሚካኤል ደጀኔ ከሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል አባል
9. አቶ ከበደ የሺጥላ አቶ ዩሱፍ አሊ ከክልል 14 ሰ/ማ/ጉ ቢሮ አባል

እነዚህ የቋሚ አማካሪ ኮሚቴ አባላት ስራቸውን እንደቀጠሉ ሌሎች በጉዳዩ አግባብ ያላቸው መ/ቤቶችና የአረጋውያን ማህበራት እንዲሁም የሌሎች ድርጅቶች ተወካዮች በስብሰባው መገኘትና መሳተፍ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ የሚቀጥሉት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ተወካዮች በተሐድሶ ድርጅት አማካኝነት እንዲጠሩ ተደርጎ በስብሰባው እስከ መስከረም 29/90 ድረስ ሰርተዋል፡፡

1. ከማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን — አቶ ግርማ ደምሴ
2. ከመድን ማህበራዊ አገልግሎት — አቶ ብንያም ሙሉጌታ
3. የወጣቶች ተወካይ — ወጣት ኤልያስ ተስፋዬ
4. ከጎንተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ — ዶ/ር ዳዊት ማሞ (አቶ ደርቤ)
5. ከተሀድሶ መምሪያ — አቶ ባሳዝን ደርቤና ወ/ሮ እስከዳር ተፈራ
6. ከትምህርት ሚኒስቴር
7. የፍቅር ስራ ልጆች የከተማ ልማት ፕሮጀክት
8. ባህልና ማስታወቂያ ሚኒስቴር
9. ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር — ዶክተር መሰረት ሽፈራው
10. የብርሃን ልጆች በጎ አድራጎት ማህበር — ካፒቴን ተስፋዬ ጫካ
11. የክልል 14 መስተዳድር ጽ/ቤት

ኮሚቴው በመጀመሪያው ስብሰባዎቹ ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ተጨማሪ አባላትና ባለሙያዎች ከየት ከየት መ/ቤትና ድርጅት እንደሚመደቡ መወሰንና እንደዚሁም የኮሚቴውን ተግባርና ሃላፊነት መወሰንና መመሪያዎቹን ማዘጋጀት ላይ ተወያይቶ ስምምነት ላይ በመድረስ ከተሐድሶ መመሪያ በቀረበለት መሰረት የመጀመሪያና ቅድሚያ የተሰጠው ስራው የነበረው

ሀ) የመስከረም 21/90 ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ቀን በዓል አከባበርን በብሔራዊና ክልል ደረጃ እንዴት እንደሚከበር ተነጋግሮ ውሳኔው ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ለ) እ.ኤ.አ. 1999 ወይም በኢት. 1991-1992 ዓ.ም. በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመት እንዲሆን በተወሰነውና ኢትዮጵያን ጨምሮ የተባበሩት መንግስታት አባል ሃገራት ሁሉ ይህንን ውሳኔ ተግባራዊ እንዲያደርጉ በተላልፈው መሰረት የአረጋውያን ተወካይ አማካሪ ኮሚቴም ከተሐድሶ መምሪያ ጋር በመመካከር ይህን ከአንድ ዓመት በኋላ የምናከብረውን የአረጋውያን ዓመት በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ በአዲስ አበባና በየክልሉ ስለሚከበርበት ጉዳይ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ድርጅቶች ተወካዮች ተጋብዘው የመጀመሪያ ዙር ጥናቶች ተጀምረዋል፡፡

የመስከረም 21/1990 ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ቀን በዓልን በተመለከተ የአረጋውያን ተወካይ ኮሚቴ ሌሎች ተጨማሪ ባለሙያዎችንና አባላትን እንዲጨመሩ አድርጎ ከተሐድሶ መምሪያ ጋር አብሮ በመስራት የኮሚቴ አባላትን በአምስት የጥናት ቡድን በመመደብ በዓሉ በብሔራዊ ደረጃ በአዲስ አበባና እንደዚሁም በክልሎች ደረጃ እንዴት እንደሚከበር፤ ፖስተሮች ፓምፍሌቶች፤ መፈክሮች፤ የራስ ቆቦች፤ ቅስቶች፤ የዜና

CCRDA

ማሰራጫዎችና ሌሎችም ሁኔታዎች እንዴት እንደሚዘጋጁ፤ በዓሉ በብሔራዊ ደረጃ የሚከበርበት ቦታ በወጪና በሌላም ረገድ የተሻለው ብሔራዊ ሎተሪ አዳራሽ እንዲሆን በመስማማትና በበዓሉ ላይ ከየመስሪያ ቤቱና ድርጅቱ የሚገኙ አረጋውያንን እንግዶቹ ብዛት ተወስኖና በተሐድሶ ድርጅት ጥሪ ወረቀቶች እንዲተላለፉ ተደርጎ በበዓሉ ላይ ንግግር የሚያደርጉ አንጋፋ አረጋውያን ተመርጠውና የሚጠይቋቸው ሰዎች ተመድበው በበዓሉ ላይ በኤግዝቢሽን መልክ የሚቀርቡ የአረጋውያን የስራ ውጤቶችን በየቦታው እየተዘዋወሩ በማፈላለግና በመጨረሻም ከተሐድሶና ከሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል በተገኘ ተሽከርካሪ እቃዎቹን የአረጋውያን የአገር በቀል ልብስ ምርቶችን ሽማግሎቹን የእርሻ ውጤቶችን ስዕሎችንና ፎቶግራፎችን ቻርቶችን መፈክሮችን ከዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ማህበር ለኤግዚቢሽኑ ተጨማሪ ድንኳን በተሐድሶ ድርጅት አማካይነት አምጥቶ በብሔራዊ ሎተሪ ግቢ ውስጥ በመትከል እነዚህ ሁሉ የኤግዚቢሽን እቃዎቹን ለህዝብ ታይተዋል፡፡ የጉባዔ ተካፋዮችም በታላቅ ደስታ ተመልክተዋቸዋል፡፡ አንዳንድ የተሸጡ እቃዎችም ሳይኖሩ አይቀሩም፡፡ በአጠቃላይ ኤግዚቢሽኑ ለአጭር ጊዜ ቢሆንም የአረጋውያንን ሙያና ችሎታ ማስተዋወቂያ ሆኗል፡፡ በኤግዚብሽኑ ላይ የክልል 14 ጡረተኞች ማህበር የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር፤ የማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን መ/ቤትና የባለስልጣኑ ጡረተኞች ማህበር የወረዳ 11 ጡረተኞች ማህበር፤ በሙሉ በተቀነባበረ የከተማ ልማት ፕሮጀክት የብርሃን ልጆች በጎ አድራጎት ማህበር፤ የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ምግባረ ሰናይ ድርጅት፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ጡረተኞች ማህበር፤ የሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል፤ ከሃገር ጥበብ ማደራጃና ከልዩ ልዩ ክፍለሃገራትና በጎ አድራጎት ድርጅቶች የኤግዚቢሽን እቃዎቹ ቀርበው ታይተዋል፡፡

በብሔራዊ ሎተሪ ስብሰባ አዳራሽ አስፈላጊው ዝግጅት ተጠናቆ መፈክሮች ቅስቶች መግለጫዎች ተዘጋጅተው በበዓሉ ላይ የመክፈቻ ንግግር የሚያደርግ ሰው ተመድቦና የዕለቱ አከባበር ፕሮግራም ወጥቶ በግምት 1500 የሚሆኑ የጉባዔ አባላት በተገኙበት የመስከረም 21/1990 ህዝባዊ ስብሰባ ግሩም በሆነ አኳኋን ከቀኑ 3-7 ሰዓት ተከናውኗል፡፡ በአዲስ አበባ ውስጥ በተለያዩ አደባባዮች የአረጋውያንን ሁኔታ የሚያንጸባርቁ ቅስቶች መፈክሮች ተደርገዋል፡፡ በዓሉ በየክልሉም በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል፡፡

በብሔራዊ ሎተሪ ለተሰበሰቡት እንግዶች ንግግር እንዲያደርጉ የተጋበዙት አንጋፋ ደራሲና አረጋዊ አቶ ማሞ ውድነህ ሲሆኑ እሳቸውም የዕለቱን በዓልና አረጋውያንን የሚመለከት ንግግር አድርገዋል፡፡ ከተሀድሶ መምሪያ አቶ መንገሻ ሃይለመለኮትና አቶ አሰፋ ባልሄር የመክፈቻ ንግግርና ልዩ ልዩ መግለጫ ከመስጠታቸውም በቀር የጉባዔ አባላትም ተሳትፎ አድርገዋል፡፡ ስለአረጋውያንና ህብረተሰቡ ትምህርታዊው ቲያትሮች ታይተው ከጉባዔ አባላት መካከል እነ አቶ ፋኖሴ ተ/ስላሴ ተመርጠው ባለአስራ ሶስት ነጥብ የአቋም መግለጫ አዘጋጅተውና ለጉባዔው በንባብ ተሰምቶ ጉባዔው በሙሉ ድምጽ ተቀብሎታል፡፡ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች እየቀረበ ስራ ላይ እንዲውል በውሳኔ አልፏል፡፡ ከነዚህም የአቋም መግለጫዎች ዋነኛውና የአረጋውያን ተወካይ አማካሪ ኮሚቴ ዋና የስራ ፍሬ የሆነው በኢትዮጵያ የሚገኙ የአረጋውያን ማህበራትና ድርጅቶች በፌዴሬሽን መልክ አንድ ብሔራዊ ማህበር ያቋቁሙ የሚለው 12ኛው የአቋም መግለጫ ሲሆን ይህም እነሆ በዛሬው ቀን በዚህ አገር አቀፍ ጉባዔ ላይ ቀርቦ ውይይት እየተደረገበት ስለሆነ ጉዳዩ ተሳክቶ በቅርብ ጊዜ ውስጥ አንድ የኢትዮጵያ አረጋውያን ድርጅቶች ብሔራዊ ማህበር እንደሚቋቋም ተስፋ አለን፡፡

በብሔራዊ ሎተሪ አዳራሽ በዓሉ ከመጠናቀቁ በፊት ለበዓሉ ዝግጅት ከፍተኛ አስተዋጽኦና ትብብር ላደረጉ ሁሉ በተሐድሶ ጉዳይ መመሪያ ሃላፊ በአቶ መንገሻ ሃይለ መለኮት የተሳትፎ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል፡፡ የመስከረም

CCRDA

21/1990 አለም አቀፍ አረጋውያን ቀን በዓል በቪዲዮ ግሩም በሆነ አኳኋን በተሐድሶ ድርጅት ባለሙያ የተቀረጸ ስለሆነ የጉባዔው አባላት ከተሀድሶ ድርጅት ጋር እየተመካከሩ ቅጂውን ለማግኘት ወይም በውሰት ወስደው በየድርጅቶቻቸው አሳይተው መመለስ ይችላሉ የሚል ግምት አለን፡፡

እንግዲህ የአረጋውያን አማካሪ ኮሚቴ የስራ ክንውን ይህን ከዚህ በላይ በአጭሩ የተገለጸውን ሲመስል የመስከረም 21/90 በአል አከባበር ሂደትና የስራ ውጤት ከበዓሉ በኋላ የተሐድሶ ጉዳይ መምሪያ ሃላፊዎችና የአማካሪ ኮሚቴው አባላት በተገኙበት ከተገመገመ በኋላ የስራ ውጤቱ ሪፖርት "ፕሮሲዲንግስ" ከነአቋም መግለጫው በአማርኛና በእንግሊዝኛ ተዘጋጅቶ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ተላልፎ ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ ይፈለግ ቢባልም እስካሁን ተዘጋጅቶ አልቀረበም፡፡ የአማካሪ ኮሚቴው በቀይ መስቀል አዳራሽ አውደ ጥናት በተቋቋመው መሰረት አሁንም ስራውን እንደቀጠለ ነው፡፡

በመጨረሻም ለጉባዔው አባላት በታላቅ ሀዘን የምንገልጸው የአረጋውያን ተወካይ አማካሪ ኮሚቴ አባላት ከሆኑት መሃከል አንዱ የጥንታዊት ጀግኖች አርበኞች ማህበር ተወካይ የሆኑት አቶ ፋኖሴ ተክለስላሴ ከዚህ ዓለም ጥቅምት 15/1990 በሞት የተለዩ ስለሆነ እኝህን ትልቅ ወንድምና አጋር ከፍተኛ ችሎታና የስራ ልምድ ያላቸውን ምሑር ማጣት ለጀመርነው የአረጋውያን ኑሮ መሻሻል እንቅስቃሴ ትልቅ ጥረት ጉዳት ስለሆነ ሁላችንም በህሊና ጸሎት እንድናስታውሳቸው አሳስባለሁ፡፡

በጥሞና ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ
ደምሴ አደፍርሰው
የአረጋውያን ተወካይ አማካሪ ኮሚቴ አባል

CCRDA

በተሐድሶ ጉዳይ መምሪያ አማካይነት በቀይ መስቀል ማሰልጠኛ አዳራሽ ከህዳር 17-19/1989 በተካሄደው አገር አቀፍ ዓውደ ጥናት ላይ የተላለፈ ባለ 12 ነጥብ የስራ ፕላን ዋና ዋና ፍሬ ነገር

1. የአረጋውያንን ቤተሰብ በመርዳት የአረጋውያን የኑሮ ሁኔታ የሚሻሻልበትን ዘዴ መፈለግ

2. ለአረጋውያን ተገቢ የሆነ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ በመስጠት ኑሯቸው የሚሻሻልበትን መንገድ ማፈላለግ

3. አረጋውያን ለወጣቱ ትውልድ የአገር ታሪክና ቅርስ ወዘተ አስተላላፊና ባለውለታ ስለሆኑ በህብረተሰቡ ውስጥ ሊከበሩና በችግራቸውም ሊረዱ የሚገባቸው መሆኑን ህብረተሰቡና ልዩ ልዩ ተቋማት ሙሉ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ የግንዛቤ ዘመቻ ማካሄድ

4. የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በልዩ ልዩ የዕድሜ ክልል ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ሊያደርጉት ስለሚገባ እንክብካቤ

5. የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎቶች በግል የስራ ድርጅቶችና በእርሻ ስራ ለተሰማራው ህዝብ እንደዚሁም በንግድና በልዩ ልዩ የግል ተዳዳሪነት ለሚጣጣሩ ሰዎች እንዲዳረሱ ማድረግ

6. ሰዎች በሚኖሩበት አካባቢና ህብረተሰብ ውስጥ ቤታቸው እንዲጠገንላቸው የጤና አገልግሎትና የበጎ ፍቃድ ወጣቶችን እርዳታ እንዲያገኙ የአካባቢ መርጃ ተቋማትን ማጠናከር

7. አሁን ተቋቁመው የሚገኙትን የአረጋውያን ማህበራትን ማጠናከር አዳዲሶች እንዲቋቋሙ ማበረታታትና አንድ አገር አቀፍ የአረጋውያን ማህበራት ብሔራዊ ማህበር እንዲመሰረት አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ

8. አረጋውያንን ደህና አድርጎ በማጥናት ደካሞችን፤ ህመምተኞችን፤ ችግረኞችን ወዘተ በመለየት ተገቢው እርዳታ እንዲደርሳቸው ማድረግ

9. አረጋውያን ባላቸው ችሎታና የስራ ልምድ በልዩ ልዩ የግልም ሆነ ባገር ግንባታ ስራ እንዲሳተፉ ማበረታታትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት

10. አረጋውያንን የሚያዋርዱና የሚያቃልሉ አነጋገሮችና አባባሎች እንዲታረሙ ከህብረተሰቡና በተለይም ከወጣቱ ትውልድ ግንዛቤ እንዲወገዱ ማድረግ

11. የአረጋውያን መብቶች የሚከበሩባቸውን የአገር ውስጥ ህግጋትና ደንቦችን ማጠናከርና የአረጋውያንን ደህንነት የሚመለከቱ የመንግስትን የማህበራዊ ፖሊሲዎችን ስራ ላይ ማዋል የአረጋውያንን ደህንነትና ሰብዓዊ መብት የሚመለከቱ የተባበሩት መንግስታትን ውሳኔዎች ማክበርና ተግባራዊ ማድረግ

12. በአገር ውስጥና በውጭ አገር በሚገኙ የአረጋውያን ማህበራት መካከል የሃሳብና የመረጃ ልውውጥ እንዲበረታታ ማድረግ

CCRDA

መስከረም 21/1990 በብሔራዊ ሎተሪ ስብሰባ አዳራሽ በተካሄደ ዓለም አቀፍ አረጋውያን ቀን በአል አከባበር ላይ የወጣ የአቋም መግለጫ

1. ስለአረጋውያን እንክብካቤ ቤተሰብ ሃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ

2. አረጋውያን ከቀያቸው ሳይርቁ እንዲረዱ ስለማድረግ

3. የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት ለህብረተሰቡ በስፋት እንዲዳረስ ስለማድረግ

4. በሰዎች መሃከል በተቻለ መጠን ያልተበላለጠ እኩል የገቢ ሁኔታ "ኢኳል ኢንካም ዲስትሪቢዩሽን" እንዲኖር ማድረግ

5. የሰዎች ካሉበት አካባቢ መፍለስና መንከራተት ቀርቶ በአካባቢያቸው በምርት ስራ የሚሰማሩበት መንገድ ይፈለግ

6. አረጋውያን የጤና አገልግሎት በቀላሉ ስለሚያገኙበት ሁኔታ ማመቻቸት

7. አረጋውያን ከዕድሜ አቻዎቻቸው ጋር የሚገናኙበት፤ ማህበር የሚመሰርቱበት ሁኔታ ይመቻች

8. የአረጋውያን የቤተሰብ ኑሮ አቋም ስለሚሻሻልበት

9. ለአረጋውያን ስለሚሰጥ ክብርና እንክብካቤ ለህብረተሰብ ትምህርት እንዲሰጥ

10. ሟሪና ደጋፊ ለሌላቸው አረጋውያን የጡረታ ቤት ስለማቋቋም

11. ለአረጋውያን የትምህርትና የስልጠና እድል ስለመስጠት

12. የአረጋውያን ማህበራት በአገር አቀፍ መልክ በፌዴሬሽን ይቋቋሙ

13. የአረጋውያንን ጉዳይ የሚከታተል በየክልሉ ድርጅት ይቋቋም

CCRDA

የቡድን ስራ

በአረጋውያን ጉዳይ ላይ የሚሰራ ቅንጅት ሊኖረው የሚችለው ቅርጽና ይዘት

ተሳታፊዎች በ4 ቡድኖች ተከፍለው ቅንጅቱ ሊኖረው ስለሚችለው አጠቃላይ ይዘት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ይዘው ተመልሰዋል፡፡

1. ስም
2. ዓላማ
3. የስራ ቦታ/አድራሻ
4. ሊሰሩ የሚገባቸው ተግባራት
5. አባል ሊሆኑ የሚገባቸው
6. የገንዘብ ምንጭ
7. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

ቡድን አንድ

ቡድኑ በአገር አቀፍ ደረጃ የአረጋውያን ማህበራት ወይም ድርጅቶች ቅንጅት አስፈላጊነት ላይ ተወያይቶ የመቋቋሙን አስፈላጊነት አምኖበታል፡፡

1. የቅንጅቱ ዓላማ

በአረጋውያን እንክብካቤ ላይ የተሰማሩ የተለያዩ ድርጅቶችን በማሰባሰብ በተጠናከረና በተቀነባበረ መንገድ ተልእኳቸውን እንዲወጡ ማድረግ፡፡

2. ዝርዝር ተግባራት

2.1 በአገሪቱ ውስጥ በገጠርና በከተማ ያሉ አረጋውያን በአጠቃላይ በቂ እንክብካቤ የሚያገኙበትን ስልት መንደፍ

2.2 የአረጋውያንን ሁኔታ በተመለከተ አገር አቀፍ ጥናቶችን ማካሄድ

2.3 በስራው ላይ ለተሰማሩ የአረጋውያን ማህበራት ድጋፍ የሚሆን እርዳታ የማሰባሰቢያ መንገዶችን መፈለግ፡፡

2.4 በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚተላለፉ አረጋውያን ነክ መመሪያዎችን ደንቦችን እንዲሁም መረጃዎችን ለአባል ድርጅቶች እንዲደርሱ ማድረግ

2.5 አረጋውያንን በተመለከተ የሚዘጋጁ አገር አቀፍ በዓላትን ዝግጅት ማመቻቸት

2.6 ከፖሊሲ አውጪዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት በማድረግ የአረጋዊያን ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ መጣር፤

2.7 የአባል ድርጅቶች የመወያያና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ማመቻቸት

2.8 የአረጋውያንን እንክብካቤ በተመለከተ ህብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ ኖሮት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ የግንዛቤ ማዳበሪያ መድረኮችን መፍጠር

CCRDA

2.9 በመሰል አገልግሎት ላይ ከተሰማሩ የውጭ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የልምድ ልውውጥ ማድረግ

2.10 አሁን ያሉትን የአረጋውያን ማህበራት ማጠናከር፤ እንዲሁም አዳዲስ ማህበራት እንዲቋቋሙ ማበረታታት፤

2.11 አረጋውያን ያካበቱትን ልምድና እውቀት ለመጪው ትውልድ የሚያስተላልፉበትን መንገድ ማመቻቸት

2.12 አረጋውያን እድሜያቸው በፈቀደላቸው አቅምና ጉልበት በገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ እየተሰማሩ አምራች እንዲሆኑ የሚያስችሉ ዘዴዎችን መሻት

2.13 ሕብረተሰቡንና ራሳቸውን አረጋውያንን በማሳተፍ የገንዘብ ማሰባሰቢያ መንገዶችን መሻት

2.14 በአረጋውያን እንክብካቤ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች የሙያ ማሻሻያ ስልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት

2.15 ቀደም ሲል የነበረው አረጋውያንን የመንከባከብ፤ የማክበርና የመርዳት ባህል ጨርሶ እንዳይጠፋና ተጠናክሮ እንዲቀጥል መንገድ መፈለግ

3. አባል መሆን የሚገባቸው

ሀ/ አረጋውያን የሚያቋቁሟቸው ማህበራት እና ለአረጋውያን የሚሰሩ ድርጅቶች (መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ) የሚያቋቁሟቸው የአረጋውያን ድርጅቶች

ለ/ አረጋውያንን ለመርዳት ፈቃደኛ የሆኑ በጎ አድራጊ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች

4. የቅንጅቱ ስም

ብሔራዊ የአረጋውያን ጉዳይ ማስተባበሪያ ቅንጅት ተብሎ እንዲጠራ ሃሳብ ቀርቧል፡፡

5. አድራሻ

አዲስ አበባ ሆኖ እንዳስፈላጊነቱ በየክልሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ሊያደራጅ ይችላል፡፡

6. የገቢ ምንጭ

6.1 የአባላት መዋጮ
6.2 ከተለያዩ አገር አቀፍና አለም አቀፍ ድርጅቶች የሚገኝ እርዳታ
6.3 ከመንግስት የሚገኝ ድጋፍ
6.4 ከግለሰቦች ወይም ከቡድኖች የሚገኝ ልገሳ
6.5 ከተለያዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች የሚገኝ ገንዘብ

7. የሚያጋጥሙ ችግሮች

7.1 የመሰባሰብ ችግር
7.2 የገንዘብ ችግር

CCRDA

7.3 የመረጃ ልውውጥ ችግር (ከስፍራ መራራቅ የተነሳ)

በመጨረሻ
እስካሁን አረጋውያንን ወክሎ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀሰው ኮሚቴ ከላይ የተዘረዘሩትን ዓላማና ተግባሮች ማካተት ከቻለ መሰረቱ እንዲሰፋ በማድረግ በቅንጅት አስተባባሪነት ሊሰራ እንደሚችል የቡድኑ አባላት ሃሳባቸው ገልጸዋል፡፡

ቡድን ሁለት

የቅንጅቱ ስም፡ በተቀናጀ ጥረት የአረጋውያን ተንከባካቢ አካል

የቅንጅቱ ዓላማ፡ ስለአረጋውያን የተደነገገውን መርሆ የተደራጁ ማህበራትን ውስጠ ደንብ በማይነካ ሁኔታ ማህበራቱን በቅንጅቱ ተሳታፊ ማድረግ

የስራ ቦታ፡ አዲስ አበባ

ሊሰሩ የሚገባቸው ተግባራት፡
በተቀናጀ መልኩ እንደየአቅማቸውና ችሎታቸው አረጋውያንን ወደተሻለ ህይወት ማምጣት

አባል ሊሆኑ የሚገባቸው፡ ለአረጋውያን ጥቅምና ደህንነት የቆመ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ግለሰቦች ቢሮ

የገንዘብ ምንጭ፡ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ ግለሰቦች እንዲሁም ከአባላት መዋጮ

ሊያጋጥመው የሚችሉ ችግሮች፡ ጥንካሬ ማጣትና የተሰፋ መቁረጥ ሁኔታ ናቸው፡፡

ቡድን ሶስት

ቡድኑ የቅንጅትን አስፈላጊነት አምኖበታል፡፡

ስም፡ የኢትዮጵያ አረጋውያን ማህበራት ህብረት

የስራ ቦታ አድራሻ፡- ዋና ጽ/ቤት አዲስ አበባ

አላማዎች፡ የኢትዮጵያ አረጋውያንን ሁኔታ ማሻሻል፡-
- የነበሩና ያሉ ድርጅቶች ማጠናከር
- ሌሎች የሚቋቋመበትን
- ታሪክና ቅርስ ባህል አውራሽ

CCRDA

ሊሰሩ የሚገቡ ተግባራት

- የማሰባሰቢያ መድረክ መፍጠር
- ስልጠናዎችን ማመቻቸት
- እርዳታዎችን መፈለግ (*Project Proposals*)
- እንዲቋቋሙ እገዛ በምዝገባና በስራ ሂደት
- *Advocacy* ንቃተ ህሊና ማዳበር
- የአረጋውያን መብቶች የሚከበሩበትን እስከ *Policy Change Negotiaton*
- የመረጃ የልምድ ልውውጦች
- ከሌሎች ሀገሮች ተመሳሳይ ማህበራት ወይም ቅንጅቶች ጋር

አባል ሊሆኑ የሚገባቸው

- በአላማው ያመኑ
- ፍላጎት ያላቸው
- በገንዘብ፤ በጉልበት፤ በዕውቀት ወይም በቁሳቁስ ለመርዳት የተዘጋጁ
- መንግስታዊ፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ለአረጋውያን የቆሙ ድርጅቶች

የገቢ ምንጭ

- የአባላት ድጎማና መዋጮ
- ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ግለሰቦች ወይም የመንግስት አካላት
- የገቢ ማስገኛ ዘዴዎች

ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

- አባላት በጋራ በየጊዜው ሊገናኙ የሚችሉበት መድረክ መፍጠር
- *Fund* የገቢ ምንጭ (ጊዜያዊ ችግር)

ቡድን አራት

የቅንጅቱ ስም፡- የኢትዮጵያ አረጋውያን ማሕበራት ፌዴሬሽን

ዓላማዎች፡-

- ዓላማውን ያስተዋውቃል
- ልምድ ይለዋወጣል
- ለአረጋውያን መብት መከበር ይቆማል
- የተሻለ ማህበራዊ ፖሊሲ እንዲወጣና ባጠቃላይ የተሻሉ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ
- መንግስትንና ህብረተሰቡን ልዩ ልዩ ድርጅቶችን በማነሳሳት አረጋውያን የሚረዱበትን ሁኔታ መፍጠር
- በማህበራት ያልታቀፉ አረጋውያን በየአካባቢያቸው የሚቋቋሙበትንና የሚታቀፉበትን ሁኔታ መፍጠር
- አረጋውያን በሴክተር በአቢይ ጉዳዮች ዙሪያ ቅንጅት እንዲፈጥሩ ማድረግ
- የስልጠናና የኢንፎርሜሽን ማዕከል መፍጠር
- አረጋውያንን በየአካባቢያቸው የሚደገፉበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ሁኔታዎችም ካሉ ማበረታታትና ማጠናከር

CCRDA

የስራ ቦታ

የፌዴሬሽኑ ቋሚ ቦታ አዲስ አበባ

ሊሰሩ የሚገባቸው

- መረጃዎች ማሰባሰብ፤ ማሰራጨት በመረጃዎች መሰረት አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ
- የሪሶርስ አጠቃቀም በተቀላጠፈና በውጤታማ መልኩ እንዲሆን ሲስተም መዘርጋት
- ፌዴሬሽኑ እንዲጠናከር ከህብረተሰቡ፤ ከመንግስት፤ ከዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶችናበራሱ ከሚደረግ ጥረት በሚገኝ ገንዘብ መጠቀም
- በማህበራት መሐከል በተወሰኑ ዓላማዎች ዙሪያ ቅንጅት እንዲኖር ያበረታታል
- አረጋውያንን ሁሉ በማሕበራት የሚታቀፉበትን ወይም ማሕበራት የሚመሰረቱበትን ሁኔታዎች መፍጠር

አባል ሊሆኑ የሚገባቸው ማሕበራት

- የመተዳደሪያ ደንብ ያላቸው
- የተመዘገቡ

ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

- ፌዴሬሽኑ በበጎ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ የአባላት በጎ ፈቃድ ማጣት
- በፌዴሬሽኑ ውስጥ አምባገነንነት ሊያስከትል የሚችል ተጽዕኖ ሊፈጠር ይችላል

CCRDA

1999 ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመት በቅንጅት ለማክበር

የካቲት 19 ና 20 ቀን 1990 ዓ.ም. የአረጋውያንን

ቅንጅት ለማጠናከር በገቡን ሆቴል የመሰብሰቢያ

አዳራሽ በተካሄደው ዐውደ ጥናት ላይ የቀረበ

የካቲት 1990 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

CCRDA

– አረጋውያን ነክ ለሆኑ ጉዳዮች በተለይ ሰብአዊ ፍላጐቶቻቸውን በማሟላትና በልማት ረገድ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ በተመለከተ በብሔራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅትን ለማዳበር ፣

– በማንኛውም ሀገር የሚገኙ አረጋውያን በሀገሪቱ ለሚገኘው የተፈጥሮ ሀብት አኩል ተጠቃሚ አንዲሆኑ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ደህንነታቸው አንዲጠበቅ አንዲሁም አረጋውያን ለኅብረተሰቡ ሁለንተናዊ ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አንዲያበረክቱ የሚያገዝ በተግባር ሊገለጽ የሚችል ፖሊሲ አንዲያወጡ መንግሥታትን ለመቀስቀስና ለማበረታታት ፣

– የአረጋውያንን ፍላጐት የጠበቀ፣ የየሀገሩን ወግና ባሕል የሚያከብር፣ የአረጋውያንን ቁጥር ዕድገት ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባና ዓለም አቀፍ የአረጋውያን መርሆያችን የሚከተል የፖሊሲ አማራጭ ለመጠቀም ፣

– ፍትሃዊ የሆነ የትምህርት፣ የሥልጠና፣ የጥናትና ምርምር አንቅስቃሴዎችን ለማጐልበት አንዲሁም አረጋውያንን በሚመለከቱ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ ሃሳብን አውቶትንና ልምድን ለመለዋወጥ የተለያዩ መድረኮችን ለመፍጠር ነው::

የቪየና ዓለም አቀፍ የድርጊት መርሃ ግብር አረጋውያንን ወደ ተሻለ ሕይወት ያሸጋገራሉ ተብለው በተመረጡ መሥመሮች ላይ ትኩረት መስጠት አንደሚገባው አስፍሯል:: በመሆኑም በሚቀጥሉት ዓመታት ትኩረት አንዲሰጣቸው የተመረጡት የዕድገት መስመሮች የሚከተሉት ናቸው::

. የቤተሰብ ድጋፍ
. ማኅበራዊ ዋስትና
. ጤናና በቂ ምግብ
. የመኖሪያ ቤትና የአካባቢ ደህንነት
. የትምህርት ዕድል ናቸው::

.../

CCRDA

በሌላ አቅጪም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ አ.አ.አ. በ1991 ባደረገው ስብሰባ አረጋውያን ያሉበትን አጠቃላይ ሁኔታ በመገንዘብ ውስጥቻቸውና ጥቅሞቻቸው አንዲከበሩላቸው የጉባዔው አባላት በስፋት አንዲወያዩበት ከተደረገ በኃላ የተባበሩት መንግሥታት መርሆዎች ለአድሜ ባለፀጎች (United Nations Principles fro Older Persons) በመባል የሚታወቁትን መርሆዎች በውሳኔ ቁጥር 46/91 አፀደቀ መርሆዎቹም ራስ መቻል ፣ ተሳትፎ፣ አንክብካቤ፣ በራስ መተማመን እና ክብር ናቸው::

1999 ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመት ፃነና ዓላማው ከላይ የተጠቀሱትን የተባበሩት መንግሥታት በተለያየ ጊዜ ያሰለፋቸውን ውሳኔዎች በተግባር አንዲተረጉሙ ለማድረግ ነው::

ለ. <u>የዓመቱ መሪ መፈክር</u>

ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመትን ለማክበር የተመረጠው መሪ መፈክር Towards a society for all ages) (ለሁሉም ትውልድ ትኩረት ይሰጥ) የሚለ ሲሆን ዓላማውም ነብረተሰቡ ጉልበቱንና ኃይሉን አስተባብሮ ለአጠቃላይ አድገት መቆም አለበት:: ይህም ማለት በአንድ ነብረተሰብ ውስጥ የሚገኝ ትውልድ በተናጠል የሚታይበት ሳይሆን የአንዱ ትውልድ አድገት ለሌላው አንዲሁም የአንዱ ትውልድ ጉዳት ለሌላው አንደሚተርፍ ታውቆ ሕብረተሰቡ በአጠቃላይ ለአድገት መነሳሳት ይገባዋል ከሚለ አስተሳሰብ የመነጨ ነው:: ስለዚህ "ለሁሉም ነብረተሰብ ትኩረት ይሰጥ" ስንል ነብረተሰቡ በራሱ ላይ ለውጥ አድርጉ አምቅ ኃይሉን ተጠቅሞ ሠርቶ ያገኘውን የሀገር ሀብት አያንዳንዱ ዜጋ አኩል ተጠቃሚ ማድረግ፣ ሰጥቶ የመቀበልን ባህርይ አንዲያጎለብት የሚያነሳሳ መፈክር ነው::

ሠ. <u>አራት አቅጪዎች ፣</u>

አላይ ለመጥቀስ አንደተሞከረው የተባበሩት መንግሥታት ያሰለፋቸውን "ዓለም አቀፍ የአረጋውያን የድርጊት መርሃ ግብር" ና "የተባበሩት መንግሥታት መርሆዎች ለአድሜ ባለፀጉች" ተግባራዊ ለማድረግ አንዲሁም "ለሁሉም ትውልድ ትኩረት ይሰጥ" የተባለውን የ1999 ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመት መሪ መፈክር በማንገብ በሁሉም አገሮች የሚገኙ መንግሥታት የተጠቀሰውን ሕብረተሰብ ለመፍጠር በአራት አቅጪዎች ላይ ትኩረት አንዲያደርጉ ያሳስባል በመሆኑም የአረጋውያን ዓመት ክብር ሲታሰብ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አራት አቅጪዎችም አብረው መታየት ይኖርባቸዋል::

CCRDA

1. <u>የአረጋውያን አጠቃላይ ሁኔታ ፤</u>

የአረጋውያን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ከመሄዱ ጐን ዚረ የሚገኙበት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታ እየቀነሰ እንዲሁም የተቋጥር ዝምድና ሥርዓቱም እየተሸረሸረና ጥብቀቱ እየላላ በመጧቱ ለተለያዩ ችግሮች የተጋለጡ መሆናቸውን የተለያዩ ጥናቶችና ዘገባዎች ያመለክታሉ:: በተለይም በታዳጊ አገሮች በአሁኑ ወቅት በከተሞች መስፋፋት፤ በሥለጧነ፤ አንዲሁም በዘመናዊ አኗኗር ምክንያት የአረጋውያን አጠቃላይ ሕይወት እየተናጋና ፈረን እየለቀቀ በመሄድ ላይ ነው:: የተለያዩ አገልግሎቶችን ፍለጋ ከገጠር ወደከተማ የሚፈለሰው የወጣት ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ በርካታ አረጋውያን በገጠር ብቸኛ ሆነዋል:: በከተማም ቢሆን ከተቋጥር ዝምድና ሥርዓት ወደ ጎዋስ በተሰብ የመለወጡ ፍጥነት ከፍተኛ ስለሆነ በዚህ ረገድ አረጋውያን የተገለሉ ናቸው አነዚህና ሌሎች ምክንያቶች ተጻምረው አረጋውያንን ወደ ድኅነት ጉስቁልናና ስደት የወሰዷቸው ስለሆነ አጠቃላይ ሁኔታቸው አጅግ አሳሳቢ አንዲሆን አድርጉታል::

2. <u>ለጣትና የአረጋውያን ቁጥር አድገት ፤</u>

የአረጋውያን ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት አያደገ መሄዱን የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ:: ይህ ቁጥር ከአንድ አገር የለጣት ደረጃ ጋር ከለተጧጧመ በርካታ አረጋውያን ለጥገኝነት ይጻረጋሉ:: ጉዳዩን ይበልጥ ውስብስብ የሚያደርገው በጣደግ ላይ በሚገኙ አገሮች ውስጥ ከአምራች ኃይል ውጭ ከሆኑት ሕፃናትና ወጣቶች በተጨማሪ የአረጋውያን ቁጥር ሲያድግ በጥገኝነት የሚኖረው ሕዝብ ቁጥር መጨመሩና አንዲሁም የአረጋውያን ቁጥር አየጨመረ በሄደ ቁጥር ወለጆቻቸውን የጣሬ የሚደገፏና የሚንከባከቡ ለጆች ቁጥራቸው መቀነሱ ነው:: ከዚህ አንፃር የነብረተሰቡንና የአረጋውያንን ፍላጉት ለማሟላት የሥራ ሥምሪት የማኅበራዊ ደህንነት፤ የትምህርት የጤናና የመሰሰሉት ፖሊሲያች ከዚህ አቅጧጧ ሊታዩና ሊቀርጹ ይገባል:: የጡረታና የማኅበራዊ ዋስትና አሰጣጥ የተሻለ ደረጃ ላይ አንዲደርስ መንግሥት ከሚሰጠው የጡረታ አገልግሎት ጉን የገለ ድርጅቶችም አገልግሎቱን አንዲያቋጥኑ ሁኔታያች መፍጠር ይናርባቸዋል::

.../

CCRDA

3. <u>የዕድሜ ቢለፀጋነት</u>

በመላው ዓለም አንዲሁም በየአገሩ የአረጋውያን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ አያደገ ከመምጣቱ ጉን የገለሰብ አረጋውያን የዕድሜ ጣሪያ አየጨመረ መምጣቱ በሌላ አቅጪ የሚታይ ጉለህ አውነታ ነው:: ይህም ማለት አረጋውያን በገለሰብ ደረጃ ሲታዩ የተሸለ ኑሮ የተመቻቸላቸውና የጤና አገልግሎት የተስፋፋላቸው በመሆኑ ረጂም ዕድሜ የመኖር አድላቸው ከፍተኛ ነው:: በተፈጠረው አመቺ ሁኔታ አረጋውያን ከረዥም አድሜ ጋር የአካለና የአአምሮ ብቃት የሚቀዳጁ ሰለሆነ በአንድ አገር ላይ የሚያበረክቱት የኢኮኖሚና የማኅበራዊ አስተዋጽአ ከፍተኛ ይሆናል:: ስለሆነም በዚህ ዘርፍ የበኩላቸውን ድርሻ አንዲወጡ ሁኔታዎች ቢመቻቹላቸው አራሳቸውንና አገራቸውን ሊጠቅሙ ይችላሉ:: 1999 ዓለም አቀፍ የአረጋውያን አመት ሲከበር አረጋውያን ከኅብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው አውቀታቸውንና ጉለበታቸውን አስተባብረው በቀጥተኛ ተሳትፎ ለዩ ለዩ አንቅስቃሴ አንዲያደርጉ ከማበረታታትና ቅድመ ሁኔታዎችን ከማሟላት ጋር አየተነፀፀረ አስፈላጊው ሁሉ መደረግ ይኖርበታል::

4. <u>በትውልድ መካከለ የሚኖር መስተጋብር</u>

ይህ ጽንስ ሃሳብ ከአመቱ መፈክር ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ያለው ሲሆን የሚያመለክተውም ትውልድ ከትውልድ ጋር ሊኖረው የሚገባው መስተጋብር ከፍተኛ መሆን አንዳለበት ያመርበታል:: ይሽውም አረጋውያን ከኅብረተሰቡ ተነጥለው የሚታዩ ሳይሆኑ ከቤተሰብ ከማኅበረሰብና ከኅብረተሰብ ጋር ያሏቸው ቁርኝት የሚዳብርበትን ሥርዓት መፍጠር አንደየነኛ ስለት ሆኖ ተቀምጧል::

ይህ አስተሳሰብ በተገቢር ሊገለጽ የሚችለው አረጋውያን በረዥም አድሚያቸው ያካበቱትን ዕውቀትና ለምድ ለተተኪው ትውልድ አንዲያካፍሉ ሲጠበቅ በአንፃሩ ደግሞ ሌላው የኅብረተሰብ ክፍል ለአረጋውያን የሚሰጠው አክብሮት ፍቅርና አንክብካቤ አንዲለግስና ሁሉም ሰዋና ተቀባይ የሚሆንበት አመቺ ሁኔታ አንዲፈጠር ማድረግ ነው::

አንገዚህ 1999 ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመት በሚከበርበት ወቅት አለይ በጽንስ ሃሳብ ደረጃ (conceptual framework) በዝርዝር የተቀመጡት "ዓለማ" "መሪ መፈክርና" "አራት አቅጪዎችን ግምት ውስጥ በማስገባትና የሚመለከታቸው ሁሉ የበኩላቸውን ጥረት

.../

CCRDA

አንዲያደርጉ ይጠበቃል:: ይህን ፅንሰ ሃሳብ ከያዝን የሚቀጥለው ደረጃ ደግሞ ለበዓሉ ዝግጅት ስኬታማነት ተግባራዊ አንቅስቃሴ ማከናወን ይሆናል::

II. የተግባር አንቅስቃሴ (Operational Framework)

የመንግሥታቱ ድርጅት አ.አ.አ. ግንቦት/1996 በ35ኛው ጉባዔ ተሰብስቦ 1999 ዓለም አቀፍ የአረጋውያን አመት ዝግጅት በተቻለ ፍጥነት አንዲጀመር ውሳኔ አስተላልፏል:: በውሳኔውም መሠረት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አማካይነት የሚንቀሳቀስ አንድ አቢይ ኮሚቴ (Focal point) ተሰይሟል:: የዚህ ዓቢይ ኮሚቴ ዋና ተግባር ከአባል አገሮች ጋር ግንኙነት በማድረግ በዓሉ በመላው ዓለም ሊከበር የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አባል አገራትም ውሳኔውን በመቀበል ዝግጅቱን በየሃገሮቻቸው መርሃ ግብር አስገብተው አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታዎች በማሟላት ላይ ይገኛሉ::

. አስተባባሪ ኮሚቴ (Focal point)

የበዓል ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ (Focal point) ማለት 1999 ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመትን በተሳካና በደመቀ ሁኔታ በመላው ዐለም አንዲከበር መንግሥታት በሃገራቸው የሚያቋቁሙት ኮሚቴ ነው አስከ ነሐሴ 1989 ዓ.ም. ድረስ ብቻ 48 አገሮች ይህን ኮሚቴ አቋቁመው ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የበዓል ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ ለከው ተመዝግበዋል:: ከአነዚህ አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ናት::

የበዓል ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ በኢትዮጵያ

የ1989 ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመት ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ በኢትዮጵያ የተመሠረተው ግንቦት 25 ቀን 1989 ዓ.ም. ነው:: ኮሚቴው የተቋቋመው ከለዩ ለዩ መንግሥታዊ መንግሥታዊ ካለሆኑ ድርጅቶች የተውጣጡ 11 አባላት የሚገኙበት ሲሆን በተለያዩ ምክንያት አስከሁን በሙሉ ኃይሉ አለተንቀሳቀሰም:: ሆኖም ከተለያዩ አገሮች ፍክለ ፕይንት ጋር የደብዳቤ ለውውጥ በማድረግ ስለበዓሉ አከባበር አንዳንድ ግንዛቤያችን ወስዷል:: በሀገሪቱ የሚገኙት ሁሉም ክለሉች በተዋረድ የበዓል ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ አንዲቋቋም ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል:: በተጨማሪም ለበዓሉ ቅድመ ዝግጅት የሚረዳ የድርጊት መርሃ ግብር ነድፏል:: ከመርሃ ግብሩ ዋነኛው በዓሉ የቀረው ጊዜ አጥር በመሆኑ በሙሉ ኃይሉ አንዲቅሰቀስና ዝርዝር

.../

የስራ ተግባራትን ለይቶ በማስቀመጥ ለተግባራዊ እንቅስቃሴ ማመቻቸት ነው።።

በኢትዮጵያ የሚከበረው ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመት በመላው ሀገሪቱ በተሳካና በደመቀ ሁኔታ እንዲከናወን በሁለት ዓቢይ ተግባሮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል።።

1ኛ/ <u>የትምህርትና ቅስቀሳ ፕሮግራም</u>

አረጋውያንን አስመልክቶ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማዳበር እስካሁን የተከናወነው ስራ ከብዙ በጥቂቱ ነው።። ስለዚህ በኢትዮጵያ የሚኖሩ አረጋውያን ያሉበትን አጠቃላይ ሁኔታ ተገንዝቦ አሁንም ሆነ ወደፊት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲወገዱላቸው እንዲሁም የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ በሚመለከት ሰፊ መሰረት ያለው የትምህርትና የቅስቀሳ ፕሮግራሞች ማካሄድ ይጠበቅብናል።። በበዓሉ አከባበር ወቅት ሊተኮርባቸው የሚገባቸው ነጥቦች ለመነሻ ያህል ከዚህ በታች የተጠቀሱት ናቸው

- አረጋውያን እንደ አምራች መታየት ሲገባቸው እውቀታቸውንና ችሎታቸውን አፍኖ በጥገኝነት እንዲኖሩ የሚያስገድዷቸው ኋላ ቀር አመለካከቶች ለማስወገድ በስዕል በድራማ በስነጽሑፍ እና በመሳሰሉት መግለጫዎች ቅስቀሳ ማካሄድ፤

  በሀገሪቱ በእንዳንድ ቦታዎች አረጋውያን በማህበርና በራስ አገዝ ቡድን እየተደራጁ በገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች እራሳቸውን፤ ቤተሰባቸውንና አገራቸውን በመርዳት ላይ የሚገኙት ለሌሎች በአርአያነት እንዲታዩ የስራ ልምዳቸውን የሚያካፍሉበት መድረክ መፍጠር፤

- በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ የተላለፉትን "ዓለም አቀፍ የድርጊት መርሃ ግብርና" "የተባበሩት መንግስታት መርሆዎች ለእድሜ ባለጸጎች" ውሳኔዎች ህብረተሰቡ እንዲያውቅ ተከታታይ ትምህርት መስጠት።።

- አረጋውያን ታሪክን ባህልንና ወግን ለመጪው ትውልድ የሚያስተላልፉ በመሆናቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ አክብረው ያቆዩልንን መዘክሮች ማስተዋወቅና ወዘተ ናቸው።።

እላይ ከቀረቡት አራት የመነሻ ነጥቦች ተነስተን ለ1999 ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመት አከባበር የበኩላችንን አስተዋጽኦ ማድረግ ነው።። ይህም ተግባራዊ ለማድረግ የሚመለከታቸውን በማሰባሰብ የበዓል ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ መፍጠርና ተከታታይ ውይይት ማድረግ፤ ውይይቱን ማዳበርና የድርጊት መርሃ ግብር መንደፍ ይሆናል።።

CCRDA

2. <u>የተግባር እንቅስቃሴ ፕሮግራም</u>

ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ የሕብረተሰቡን የአመለካከት ግንዛቤ ከማስፋት ጎን የ1999 ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመት ሲከበር ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች በተጓዳኝ መካሄድ መቻል አለባቸው፡፡ ይህንንም እውን ለማድረግ በተግባር ሊገለጹ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን መንደፍ ይሆናል፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶች የአረጋውያንን ፍላጎት የሚያሟሉ ዘላቂና በርካታ ተጠቃሚዎችን የሚያቅፉበት ሊሆን ይገባል፡፡ ለፕሮጀክቶቹ የሚሆን ገንዘብ ከመንግስት ወይም ከተለያዩ ዓለም አቀፍና አገር በቀል ድርጅቶች ለማግኘት ጥረት ማድረግ፡፡

በተጨማሪም በተበበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ የተላለፉትን ዓለም አቀፍ የድርጊት መርሃ ግብርና የተባበሩት መንግስታት መርሆዎች ለዕድሜ ባላጸጎች ውሳኔዎች በሀገራችን ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስ አስፈላጊ ነው፡፡

<u>ማጠቃለያ</u>

ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመት 1999 በደመቀ ሁኔታ ለማክበርና ወደፊትም የአረጋውያንን ህይወት ወደተሻለ ደረጃ ለመለወጥ አስፈላጊው ዝግጁነት ከተፈጠረ በርካታ ስራዎችን ለመስራት የሚከለክል ነገር አይኖርም፡፡ ዋናው ነገር አረጋውያን ያሉበትን አጠቃላይ ሁኔታ በመገንዘብ በዓለም አቀፍና በብሔራዊ ደረጃ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ መሆኑን አውቆና የሕብረተሰቡን የግንዛቤ አድማስ በማሳደግ ይህን ጅምር ስራ በቀጣይነት ማካሄድ ነው፡፡ ከአረጋውያን ጋር የሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ማህበራትና ግለሰቦች ከሁሉም በላይ ደግሞ ሕብረተሰቡ ጥብቅ የስራ ግንኙነት (*Net work*) በመፍጠር ወደተፈለገው ግብ ማምራት ሃላፊነት አለባቸው፡፡ በአገሪቱ ውስጥ የሚደረገውን አጠቃላይ የበዓል ዝግጅት በአስተባባሪነት የሚመራው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰብሳቢ የሚሆንበት <u>የብሔራዊ የበዓል ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ</u> ነው፡፡ አስተባባሪ ኮሚቴው በድርጅትም ሆነ በግለሰብ ደረጃ በአከባቢው ላይ ተሳታፊ ለመሆን የሚፈልጉትን ሁሉ በማስተባበር በቅንጅት ለመስራት ከፍተኛ ፍላጎት አለው፡፡ የኮሚቴው አድራሻ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፡፡

በተጨማሪም በድርጅትም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ብሎም ስለ ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመት የተሻለ እውቀትን ለማግኘትና ግንዛቤን ለማጎልበት የሚፈልጉ ሁሉ አስፈላጊውን መጻጻፍ እንዲያደርጉ ከዚህ ጋር የቀረበውን አድራሻ መጠቀም ይችላሉ፡፡

በፕሮግራሙ ላይ ተሳታፊዎች የ1999ን አከባበር በተመለከተ በቡድን ተወያይተው ሃሳብ እንደሚያቀርቡ ተመልክቶ የነበረ ቢሆንም ተሳታፊዎች ቀደም ሲል ለተቋቋመው ብሄራዊ የበዓል ዝግጅት ኮሚቴ በግልም ይሁን በቡድን ሃሳቦችን ስለምንሰጥ እዚህ ማንሳቱ አስፈላጊ አይደለም ሲሉ ተስማምተዋል፡፡

CCRDA

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የማኅበራዊ ደህንነት ፖሊሲ አደገት አስተባባሪ መምሪያ ዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመት በተሰኪ ሁኔታ አንዲከበር ለዮ ዝግጅት በማካሄድ ላይ ይገኛል:: በውስጡም ከመላው ዓለም ጋር የሥራ ግንኙነት የሚኖረው የበዓል አስተባባሪ ኮሚቴ (Focal Point) አየቅርአለ:: ከሁሉም አገሮች ጋር የሚገናኝበት Count Down to 1999 የተሰኘ ለሰን አለው::

አድራሻው፤

. Department for Policy Coordination and Sustainable Development
. Division for Social Policy and Development the United Nations Focal Point for the International Year of Older Persons 1999
. Room DC2-1358,2 UN Plaza, NewYork, NY 10017
Fax:(212) 963-3062

CCRDA

ረቂቅ ቻርተር

ለሁሉም ትውልድ ትኩረት ይስጥ በሚለው መሪ መፈክር መነሻ የአሜሪካን ጡረተኖች ማኅበር ጽ/ቤት ለዓለም አቀፍ የአረጋውያን ዓመት የሚያገለግል ረቂቅ ቻርተር አዘጋጅቷል:: ረቂቁን በመላው ዓለም የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ድርጅቶች አስተያየት አንዲሰጡበት አስተላልፏል:: የቻርተሩን ረቂቅ በጣየት የተጠየቀውን አስተያየት ለመስጠት የሚከተለው አድራሻ መጻፃፍ ይቻላል::

Charlotte Nusberg
AARP
601 E St. NW
Washington, DC. 20049
USA
Fax: 202/434-6408

CCRDA

Coalition'99

አ.ኤ.አ. በ1995 ኮፐንሃገን ላይ ዓለም አቀፍ የማኅበራዊ አድገት ጉባዔ በተካሄደበት ወቅት መንግሥታዊ ያልሆኑ ለዩ ለዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በጄህነት በሥራ ቅጥርና በማኅበራዊ ውህደት ችገሮች ላይ ባቀረቡት የመፍትሔ ሃሳብ ላይ በተነሳው ክርክር ኮአሊሽን 99 ሊፈጠር ችሏል:: በአሁኑ ጊዜ ይህ ድርጅት አለም አቀፍ የአረጋ ውያንን ዓመት ከሁሉም መንግሠታዊ ከለሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በደመቀ ሁኔታ አን ጻከበር ፕረት በማድረግ ላይ ይገኛል:: በመላው ዓለም የሚሰራጭ **Coalition ,99 up date** የተሰኘ ለሲን አለው::

አድራሻ፤

E.K.Mullen, International Activities
American Association of Retired Persons
601 E Street, N.W.
Washington, DC 20049
USA

CCRDA

የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች የውሳኔ ሃሳብ / የአቋም መግለጫ

በሁለቱ ቀናት በተካሄደው ሰፊ ውይይት መሰረትና በቡድን ስራዎች በቀረቡት ስራዎች መሰረት የተሳታፊዎች የውሳኔ ሃሳብ እንደሚከተለው ተጨምቆ ቀረበ፡፡

1. የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በኢትዮጵያ የአረጋውያን ጥምረት/ውህደት መመስረት አስፈላጊነቱን አምነው ተቀብለዋል

2. የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች አሁን ያለው የአረጋውያን አሰባሳቢ ቋሚ ኮሚቴ ቅንጅቱን የመመስረት ሃላፊነቱን ወስዶ መንቀሳቀስ እንዳለበት ተስማምተው ተቀብለዋል

3. የክልል ተወካዮችን በአረጋውያን አሰባሳቢ ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ እንዲሳተፉ በማድረግ ኮሚቴውን ለማጠናከር ተስማምተዋል

4. የአረጋውያን አሰባሳቢ ቋሚ ኮሚቴው የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎችን ያወጡትን የአቋም መግለጫ ለቅንጅት መስራች ኮሚቴው የስራ መንደርደሪያ እንዲሆን በሚገባ አርቅቆ እንዲያቀርብ ተስማምተዋል፡፡

5. የአረጋውያን አሰባሳቢ ቋሚ ኮሚቴ ያረቀቀውን የአውደ ጥናቱ የአቋም መግለጫ አስተያየት እንዲሰጥበትና ውይይት እንዲደረግበት ለተወካዮች ሁሉ እንዲያስተላልፍ ተስማምቷል፡፡

6. ሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል የዚህን አውደ ጥናት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለተሳታፊዎች ሁሉ እንዲያድል ተስማምተዋል፡፡

7. የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በአረጋውያን አሰባሳቢ ቋሚ ኮሚቴ አስተባባሪነት 1999 በደመቀና የሁሉም ተሳትፎ ባለበት ሁኔታ ለማክበር ተስማምተዋል፡፡

8. አሁን የተጀመረው ቅንጅት የመፍጠር ሂደት ለማዳበር የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች እንደገና መገናኘት አስፈላጊ መሆኑ አምነው ተስማምተዋል፡፡

CCRDA

የዓውደ ጥናቱ ግምገማ

ለተሳታፊዎች የሚከተሉት ጥያቄዎች በመጠይቅ መልክ ቀርበው መልስ ከሰጡት 34 ተሳታፊዎች ተጨምቆ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. ይህ ዓውደ ጥናት ከስራዎ ጋር ያለው ግንኙነትና ለስራዎ የሚያስገኘው ጠቀሜታ

   29 ተሳታፊዎች በጣም ጥሩ እንደነበር ሲያመለክቱ 5 ተሳታፊዎች ደግሞ ጥሩ እንደነበር አመልክተዋል፡፡

2. ዓውደ ጥናቱ የታቀደለትን ዓላማ ለማሳካት መቻሉን በደረጃ ቢያስቀምጡት
   15 ተሳታፊዎች ከፊሉን አሟልቷል ብለዋል
   19 ተሳታፊዎች በሙሉ አሟልቷል ብለዋል፡፡

3. በአውደ ጥናቱ የተሳተፉት ተሳታፊዎች ስብጥር በእርስዎ አስተያየት
   22 ተሳታፊዎች ስብጥሩ ትክክለኛ እንደነበር ገልጸዋል
   11 ተሳታፊዎች ስብጥሩ በመካከለኛ ደረጃ ሊታይ እንደሚችል የገለጹ ሲሆን
   1 ተሳታፊ ተሳታፊዎች እነማን እንደነበሩ ስላላወቁ ለመናገር እንደማይችሉ ገልጸዋል፡፡

   ለሶስተኛው ጥያቄ መልስዎ ያልተስተካከለ ነው የሚል ከሆነ በተጨማሪ ሊገኙ ይገባቸዋል የሚሏቸውን ተሳታፊዎች ከዚህ በታች ቢዘረዝሯቸው

   የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ለምሳሌ ዓይነ ስውራን፣ የስጋ ደዌ ህሙማንና መስማት የተሳናቸው፡፡

   ከሁሉም የክልል መስተዳድሮች የሚመለከታቸው አባላት መሳተፍ ነበረባቸው ሲሉ ተጨማሪ አስተያየታቸውን ገልጸዋል፡፡

4. ዓውደ ጥናቱ የተጠቀመባቸው የመማማሪያ ዘዴዎች ተሳታፊዎችን በማሳተፍ በኩል?
   23 ተሳታፊዎች በጥም ጥሩ እንደነበር አመልክተዋል፡፡
   8 ተሳታፊዎች አሳታፊነቱ መካከለኛ እንደነበር አመልክተዋል፡፡
   2 ተሳታፊዎች አሳታፊነቱ እጅግ አነስተኛ እንደነበር አመልክተዋል፡፡

5. ተመሳሳይ ዓውደ ጥናት የሚካሄድ ቢሆን ሊሻሻሉ ይገባቸዋል የሚሏቸውን ነጥቦች ቢዘረዝሩ ለሚለው ጥያቄ ከጥቂት ተሳታፊዎች የሚከተሉት ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

- በሰዓት አከባበር ረገድ ጊዜው አጭር ሆኖ ሳለ የሃሳቦችን መንሸራሸር ቆረጥ ቆረጥ አለማድረግ
- ተሳታፊዎች የመጡበትን ቦታ ለመግለጽ ዕድል አላገኙም በሰዓት እጥረት ምክንያት ስለዚህ ጊዜው መጨመር አለበት

CCRDA

- የሚሰጠው ትምህርት በቅድሚያ በጽሁፍ የምንወያይበትን ነጥቦች አስቀምጦ በነዚህ ነጥቦች ላይ መወያየት ነበረብን
- የአውደ ጥናቱ አቅራቢዎች በብቸኝነት ፕሮግራማቸውን እንዲያሳኩ አለበለዚያ ደባል ሁኔታዎች ሊቀርቡ አይገባም
- የሚቀርቡ ጥናታዊ ጽሁፎች *extract (abstract)* ቢኖሩ
- በዓውደ ጥናት ዓላማው ላይ ትኩረት በመስጠት በውይይት ዳብሮ በተመደበለት ጊዜ ቢከናወን
- አጀንዳው በቅድሚያ ቢታወቅ ብዙ ሃሳብ ይዞ ለመምጣት ከማስቻሉም በላይ ጊዜ ይቆጥባል
- ተሳታፊዎች በቅድሚያ ቢተዋወቁ መፈራራትና መተፋፈር ሳይኖር ተሳትፎን ያበረታታል
- የስብሰባው ሊቀመንበሮች የጊዜን ጉዳይ በደንብ ቢያከብሩና ከአጀንዳ ውጪ ጊዜ ባያጠፉ
- አጭር የትምህርት አቀራረብና አሰጣጥ ዘዴ ቢሆንና ለቡድን ውይይትና ለ*Presentation* እንዲሁ አጠቃላይ ውይይት ጊዜ ቢኖር
- የልምድ ልውውጦች ዝቅተኛ ነበር ለእንደዚህ ዓይነት በጎ ተግባር ፍላጎትን ለማነሳሳት ልምዶች ከየድርጅቶችና ከየማህበሮች በግል የቀረቡ ቢሆን የተሻለ ነበር፡፡
- ትንሽ ሰዓት የሚጨምርበት ሁኔታ ቢፈጠር
- አውደ ጥናት የሚደረግበት ነጥብ ተለይቶ ለተሳታፊዎች በግልጽ ቢታወቅ
- በመጀመሪያ ደረጃ የአውደ ጥናቱ አሰጣጥ በተስተካከለ ቋንቋ መቅረብ አለበት ይህም ሲባል ሁሉንም በሚያሳትፍ ቋንቋ
- ለናሙና ያህል ረዥም ዕድሜ ካላቸው ዕድሮችና ሌሎች ማህበራት ተጋብዘው ስለአረጋውያን ምን ሊያበረክቱ እንደሚችሉ ቢማሩ
- በየአካባቢው ያሉትን የአረጋውያን ኮሚቴ በበለጠ ታውቀው መሳተፍ አለባቸው
- እያንዳንዱ አባል ወክሎ የመጣበትንና ራሱን በመጀመሪያ የማስተዋወቂያ መድረክ ማመቻቸት ቢቻል
- ጊዜን በአግባቡ መጠቀም
- የአውደ ጥናቱ አዘጋጆች ፕሮግራሙ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ቢመሩና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ትክክለኛ ውሳኔ በመስጠት ተሳታፊዎችን ከመደናገር ቢያድኗቸው፡፡
- የሰዓት መጨናነቅ ታይቷል የተመደበለት ጊዜና የአውደ ጥናቱ ሂደት ተመጣጣኝ ስላልሆነ ለወደፊቱ ቢታሰብበት ጥሩ ነው፡፡
- ዓውደ ጥናቱን መሰረት ያደረጉ ጽሁፎች ለዓውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በጽሁፍ መልክ ቢሰጥ የበለጠ ያማረ ይሆናል፡፡
- የተሳታፊዎች ስብጥር ከሁሉም ክልል የሃሳብ ልዩነት ስላለ በቂ ጊዜ መስጠት
- ጊዜ ምን ጊዜም በስብሰባ ጊዜ አጭር ነው ነገር ግን የተሰጠውን ጊዜ አዘጋጆች በተመኑት መሰረት መጠቀም መቻልና ሃሳብ መደጋገምና ማሰባሰብ መቻል
- የጊዜ ማጠር እየተከሰተ ነው ለወደፊት የጊዜ ሁኔታ ሊታሰብበት ይገባል፡፡
- ቅድመ ዝጅግቱ ማለት የወርክሾፑን ዓላማ ቁልጭ አድርጎ ማስቀመጥ ስለወርክሾፑ የሚጠበቀውን አጠቃላይ ሂደት እንደመንደርደሪያ ሃሳብ መስጠት
- ተሳታፊዎች እርስ በርሳቸውና ስለስራቸው በግልጽ የሚነጋገሩበትና የሚተዋወቁበት ዘዴ ቢቀየስ
- በጉባኤ ወቅት አስፈላጊ ባልሆኑ ርዕሶች ባንጨቃጨቅ

CCRDA

- አረጋውያን የሚለው አባባል ለወንድ ብቻ ስለሆነ ሌላ አጠቃላይ የሆነ ስም ካልተገኘ በስተቀር አረጋውያት የሚለው ቃል ቢጨመርበት
- ጊዜው የሚሰፋበት መንገድ ቢመቻች ጊዜ የለም እየተባለ ጥሩ ጥሩ ሃሳቦች ሳይሰነዘሩ ከሚቀሩ አምሽቶም መውጣት ቢቻል
- የተሳታፊ አባላትን አድራሻ ስም የመጠበት ክልል በታይፕ ተጽፎ ለየተሳታፊው ቢሰጥ ከቅንጅት ክፍሉ አንዱ ይሆን ነበር፡፡
- ተሳታፊዎች ስለሚሳተፉባቸው ነጥቦች በቅድሚያ ቢያውቁ በተሳትፎ በኩል የበለጠ ውጤታማ ሊሆን ይችላል
- አላማው በሀገራችን የሚገኙትን ችግረኛ አረጋውያንን ሊወክል የሚችል ተወካዮችን ያካተተ ቢሆን
- በሰዓት አጠቃቀም ላይ ያለውን ችግር ለመቀነስ መወያያ የሚሆኑ ርዕሶች ከተደረጉት ውይይቶች አኳያ በቅድሚያ ቢቀርቡ

6. ተጨማሪ አጠቃላይ አስተያየት ካለዎት ከዚህ በታች ያለውን ቦታ ይጠቀሙ

- የተሳታፊዎች ዝርዝር በጥባዔው ላይ ቢገለጽና ማስታወቂያ ቢደረግ ከተቻለም ቀደም አድርጎ በጽሑፍ ቢግለጽ
- ንግግር የሚያደርጉ አባላት ቀደም አድርጎ ቢገለጽላቸው
- እኔ ከአዲስ አበባ የመጣሁ ተሳታፊ ነኝ ወደ ሂሳብ ክፍል ሂዱ ሲባል የምከፈለው ነገር ይኖራል ብዬ ነበር የጠበቅሁት ለትራንስፖርት ተብሎ የተከፈለው ሰላሳ ብር ብዙ ነው፡፡ ተማርን በቁም ነገር ተነጋገርን በላን ጠጣን በዚያ ላይ ደሞ ለትራንስፖርት (ለአዲስ አበባ ተሳታፊዎች ማለቴ ነው) ወጪ መደረጉ የበዛ ይመስለኛል፡፡
- ከክልሎች የመጡ ተወካዮች በቂ ጊዜ አላገኙም፤ አጀማመራቸውን፤ አመሰራረታቸውን ሁሉ በጥባዔው ማስቀመጥ ያለመቻላቸው ትልቅ ችግር ሆኗል እንጂ በተረፈ በዚሁ ዓይነት ቀጥሉበት
- ስብሰባው በጣም ጠቃሚ ነው
- ይህ ዓውደ ጥናት እጅግ አርኪ ሆኖ ያገኘሁት በአገር አቀፍ የሚቋቋመውን የአረጋውያን ማህበራት በማስተባበር ዘላቂ የሆኑ መፍትሄዎችን አረጋውያን ራሳቸውን በራሳቸው የሚረዱበትን መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑት ለሚያደርጉት እርዳታ አስተባባሪ መሆን ስለሚችል ጠቃሚ ዓውደ ጥናት እንደሆነ ተገንዝቤአለሁ
- አዘጋጁ ክፍል ሃላፊነቱን በብቃት ተወጥቷል ማለት እችላለሁ
- የአዳራሽና የምግብ ወጪን ለመቀነስና በስፋት አባላትን ለማስተናገድ እንዲቻል በሌሎች በአነስተኛ ዋጋ በጥራት የሚዘጋጅበት መንገድ ቢፈለግ
- አወያዮች በመወያያ ርዕሶች ላይ ብቻ እንዲተኮር ቢያደርጉ ጊዜን አላግባብ ከማባከን ያድናል
- ለወደፊቱ ከዚህ የበለጠ እንደምትሰሩ እምነቴ የጸና ነው፡፡
- አስተማሪዎች የተሳታፊዎችን ሃሳብ ባይገቱ (ለተወሰነ ሰው ብቻ እድል ባይሰጡ) የአረጋውያን በብሔራዊ ደረጃ፤ በክልልና ብሎም በወረዳ ደረጃ ሳይቀር የሚደራጁበትን መንገድ መቀየስ ተገቢ ነው፡፡ ለዚህም በ1984 ጀምሮ በተከታታይ የተደረጉት መሰል ዓውደ ጥናቶች የዛሬውን ጨምሮ ያደረጉት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይም አስተባባሪው ኮሚቴ እስካሁን ሲያደርገው የቆየው ተግባር የሚያበረታታ ስለሆነ በርቱ፡፡

CCRDA

- ተሳታፊዎችን ያምታቱ አጀንዳዎች በቀን ሁለት ታይተዋል፡፡ አውደ ጥናቱ ብዙ ጊዜ ባለቤት እያጣ ስለነበር እንዲህ ዓይነት ችግሮች ቢወገዱ በተጨማሪ ጊዜ አጠረ መርሆ ባይሆን ጥሩ ነው
- ከዚህ በኋላ በሚዘጋጁት አውደ ጥናቶች ላይ የሚቀርቡት ትምህርቶች በአረጋውያን እንክብካቤ ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶችን የሚያሳትፍ ቢሆን ይመረጣል
- ሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናልና ገለጻውን በማድረግ የተሳተፉት ሁሉ ልባዊ ምስጋና ይገባቸዋል አስተሳሰባችንን ለተቀስቀሰና ለከፍተኛ ዓላማ እንድንነሳሳ አድርገዋልና
- የዚህ አይነት አውደ ጥናት አስፈላጊ መሆኑን አምናለሁ ሆኖም ወደ መጨረሻው አካባቢ ግን የተቋቋመን ነገር በግድ እንዲቀጥል ተሳታፊዎች ላይ ጫና መደረግ አልነበረበትም በተማርነው መሰረት እንድንወስን ቢደረግ ለወደፊቱ ትምህርት ይሰጣል እላለሁ
- በእውነት ከሆነ ይህ አውደ ጥናት በጣም ብዙ ተፈላጊ የሆኑ ነጥቦችን አጠቃሏል፡፡ በጣም መበረታታት አለበት በረዥም ጊዜያት ግንኙነት ብቻ ሳይሆን በቅርብ ጊዜያት እንደገና ተገናኝቶ የተለያዩ ትምህርቶችን ማካተት አለበት
- ቅንጅት የመፍጠሩ ሁኔታ በትእግስት ከተከናወነ በማህብረሰቡ ዘንድ ወደፊት ከፍተኛ ድጋፍ ሊያገኝ ይችላል፡፡
- የአረጋውያን ማህበር ለማቋቋም ጊዜ የማይሰጥ ስለሆነ በመርህ ደረጃ ሃሳቦች ፈልቀው በየክልሉና ወረዳው ያሉት አረጋውያን ተወያይተው ነጥቦቹ የአረጋውያን ደንብ ሆነው እንዲጸድቁ ቢደረግና ራሳቸው ተሳታፊ ሆነው የሚያጸድቁት እንዲሆንና በመንግስት ደረጃም ትኩረት እንዲደረግበት ግፊት እንዲያደርጉ ቢሆን
- በቅንጅት መስራት ጠቀሜታ አለው ይሁን እንጂ ቅንጅቱ ያስፈልጋል ከተባለ ከታች ወደላይ እየመጣ መስራት የሚገባው ነው
- የአሁኑ ጊዜያዊ ተብሎ ይደራጅ እንጂ በቅንጅት ለመቀጠል ከተፈለገና ውጤታማ ለማድረግ እያንዳንዱ ድርጅት ከአባላቱ ጋር ተወያይቶና ተረዳድቶ ግንኙነትን መፍጠር እንዳለበት ነው
- በአነስተኛ ወጪ ረዘም ላለ ጊዜ ልንጠቀምበት የምንችለው ቦታ ቢፈለግ ለወደፊቱ ተመሳሳይ አውደ ጥናት ቢደረግ
- አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሳያስተላልፉ ማለፍ አይገባም፡፡
- በሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል በኩል ጠቃሚ የሆኑ ማቴሪያሎችና አረጋውያንን የሚመለከቱ የካሴት ፊልሞች በተሳታፊዎች አድራሻ ቢላኩ በተለይ የአረጋውያንን በዓል በክልል ደረጃ ለማክበር ጠቃሚ ይሆናል
- ይህ አውደ ጥናት የተለያዩ ተሞክሮዎችና የስራ ልምዶችን እንድናካብት ያደረገ አመርቂ የሆነ ዝግጅት ስለነበረ ይበልጥ እንዲጎለበት በየጊዜው መሰል አውደ ጥናቶች እንዲዘጋጁ ይደረግ
- ከተሳታፊዎች የሚመጡ ጥያቄና አስተያየቶች በቂ ጊዜ አግኝተው መብላላት አለባቸው
- የቅንጅት ምስረታ ከሁሉም ማህበራት ተመርጠው መሳተፍ በመጀመርያ ኮሚቴዎች እንዲወያዩበትና አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ

ድርጅቱ ለማሰባሰብ ያደረገው ጥረት ከፍተኛ አድናቆት አለው ለወደፊቱም የሚመለከታቸውን በማሰባሰብ ቅንጅት እስከተቋቋመ ድረስ ይቀጥል በበኩሌ ጥሩ ግንዛቤ አግኝቻለሁ

CCRDA

- አሁንም የጊዜ ጉዳይ በመሆኑ የማህበራት ተወካዮች የየራሳቸውን የስራ ውጤትና የማህበራቸውን እድገት ደረጃ ባጭር ባጭሩ ለመግለጽ የሚችሉበት ሁኔታ ለወደፊት ቢመቻች
- ባጠቃላይ በጣም ጥሩ ነበር አንዳንድ ችግር ቢፈጠርም ተፈቷል፡፡ ለወርክሾፑ የተጨነቃችሁበትን ያህል ለወደፊቱ ለፌዴሬሽኑ ምስረታ እንደምትጨነቁበትና ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ እንደምትፈጥሩ ሙሉ እምነት አለኝ
- ቅንጅቱ የደረሰበት ደረጃ እንዲታወቅ የመረጃ ልውውጡ ፈጣን ቢሆን ይመረጣል፡፡
- የቅንጅቱ ጉዳይ ግቡን እንዲመታ ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል
- የተሰጠው ትምህርትና የተደረሰበት ጥምረት/ውህደት በጣም ጠቃሚና ስንመኘው የነበረ ስለሆነ በክልል 14 መስተዳድር የጡረተኞች መረዳጃ ማህበር ስሜት በጣም የላቀ ነው
- በመጀመሪያው እለት እንዲሁም በሁለተኛው ዕለት ተሳታፊዎች ሃሳባቸውን አንዳመቁ ሄደዋል የሚል እምነት አለኝ
- የሰብሳቢዎች መለዋወጥም ችግር ስለሚፈጥር የተወሰኑ ሰዎች ተመድበው ቢሰጡ የተሻለ ይሆናል ወደፊት ለሚደረገው ስብሰባም ከአጀንዳ ውጪ በተጣማሪነት የሚመጡት ግራ የሚያጋቡ ስለሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ ስብሰባውን ውጤታማ ያደርጋል
- አብዛኛው ተሳታፊዎች የጡረተኞች ተወካዮች ናቸው ማተኮር ያለብን በማህበረ ሊደራጁ ያልቻሉ ወይንም ተወካይ የሌላቸውን የታረዙ፣ የተቸገሩ በርካታ አረጋውያን ያሉ ስለሆነ እነሱን የሚወክል ባለው አደራጅ ኮሚቴ መታቀፍ አለበት፡፡ ይህንን ስል አሁን የተደራጁት ጡረተኞች በዚህ ረገድ ያላቸውን ሚና ወደጎን በመተው አይደለም

የአውደ ጥናቱ መዝጊያ

ሚ/ር ጀፍሪ ኦዶኖሂ የሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል ፕሮግራም ዳይሬክተር ባሰሙት የመዝጊያ ንግግር የአረጋውያንን ጥምረት የመፍጠር ቀደም ሲል የተጀመረ ሂደት እንደነበርና አሁንም በሂደቱ መካከል ነን ብለዋል፡፡

1999ን ጨምረን የተነሱት የመነጋገሪያ አጀንዳዎች ከፍተኛ እንቅስቃሴና እድገት የማሳየታችን ማስረጃዎች ናቸው፡፡ የቅንጅት ጽንሰ ሃሳብ ምን እንደሆነና በኢትዮጵያ ያለውን መልክ ለማየት ሞክረናል፡፡ ይህ የመጀመሪያ ሙከራችን ሲሆን የመማሪያ መድረካችንም ነው፡፡ ማድረግ የነበሩብን ብዙ ነገሮች እንደነበሩ ተረድተናል፡፡ ቢሆንም ተሳታፊዎች በቅንነት የግምገማ አስተያየታቸውን እንዲሰጡን እንጠይቃለን፡፡

የተሳታፊዎች ስብጥር በርካታ በሆነበት ሁኔታ ቅንጅትን መፍጠር ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነና በዚህ ላውደ ጥናት ላይ የተከሰቱትን አይነት የሃሳብ ልዩነቶች መከሰታቸው ባህሪያዊ በመሆኑ ተሳታፊዎችም ይህንን ከግንዛቤ እንዲያስገቡ ጠይቀዋል፡፡

በመጨረሻም ተሳታፊዎችን ጊዜያቸውን ሰውተው ለዚህ ጠቃሚ ጅምር ላበረከቱት ጠቃሚ ሃሳቦች ካመሰገኑ በኋላ የዚህ አውደ ጥናት ሪፖርት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተሰርቶ ለተሳታፊዎች እንዲደርስ ለማድረግ ጥረት እንደሚደረግ አስታውቀዋል፡፡

CCRDA

አገር አቀፍ የአረጋውያን ጥምረት አውደ ጥናት
የካቲት 19-20/1990
ግዮን ሆቴል አዲስ አበባ

የተሳታፊዎች ሥም ዝርዝርና አድራሻ

ተ.ቁ	መሉ ሥም	የመጡበት መ/ቤት	ስልክ ቁጥር	ፖ.ሳ.ቁ	የሥራ መደብ
1	አሸናፊ ደስታ	ክልል 14 ጡረተኞች መረዳጃ ማኅበር	114272	29052	ተ/ሊቀመንበር
2	ኢትዮጵያ ወንጌል	ኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር	519144	195	የድ/አደጋ ዕርዳታ ሠራ
3	ፍሰሐ አላዛር	በመሉ የተቀነባበረ ዘዴ የከተማ ልማት ፕሮጀክት	156375	6889	ማህበራዊ አገልግሎት
4	ሽፈራው በላይነህ	የብርሃን ልጆች በጎ አድራጎት ማኅበር	154628	197	ፕሮግራም አስተባባሪ
5	አሰፋ ውብነህ	ጎንደር ጡረተኞች ማኅበር	-	902	ሊቀመንበር
6	ብርሃኑ ወርቁ	ገንዘብ ሚኒስቴር ጡረተኞች ማኅበር	-		አረጋውያን ኮሚቴ
7	ግርማ መንግስቱ	ብስራት የልማትና በጎ አድራጎት ማኅበር	189862	32959	ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
8	ናዲያ ወባር	የካናዳ ሐኪሞች እርዳታ ማኅበር	653944	2555	ተራድኦ አሰባሳቢ
9	ዓብይ መኩሪያ	ክልል 14 ጡረተኞች ማህበር	112472	29052	የዋስትና ጋዜጣ ዋና አ
10	ጎይትኦም አብርሃም	በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሕጻናትና ቤተሰብ ጉዳይ ኮሚሽን	552216	30269	ፕሮግራም መሪ
11	እስክዳር ተፈራ	ክልል 14 ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ	152692	30269	ሕዝብ ግንኙነት
12	ጌታሁን አበራ	ወረዳ 11 ጡረተኞች ማህበር	111968	-	ሊቀመንበር
13	የሱፍ አሊ	ክልል 14 ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ	513372	3328	የአረጋውያን ኤክስፐርት
14	አባ ኃ/ጊዮርጊስ ኃይለሚካኤል	ቤተ ሳሊሆም	-	-	አስተዳደር
15	ሰለሞን ከበደ	ዞን 6 ሠ/ማ/ጉ መምሪያ	340017	23	የአረ/የአካል ጉዳተኞች ኃላፊ
16	ሃይማኖት መኮንን	መልካም እረኛ እህቶች ማኅበር	160437	6558	የአረጋውያ ፕሮግራም
17	ኃይሉ ታፈሰ	ኢየሩሳሌም ህፃናት ማሳደጊያ ድርጅት	611093	41742	የፕሮግራም ኦፊሰር
18	ሸዋ ፀሐይ በልሁ	ፓክት ኢትዮጵያ	511955	13180	ፕርግራም ኃላፊ
19	ብርሃኑ ማሞ	ዞን 6 ሠ.ሚ.ጉ መምሪያ	340108	23	መምሪያ ኃላፊ
20	ፀጋዬ ቸርነት	ፓክት ኢትዮጵያ	511955	30621	ዳይሬክተር
21	ኢብራሂም ሰይድ	ክልል 14 እስልምና ጉዳይ ቢሮ	752291	-	የወጣቶች ሊቀመንበር

CCRDA

22	ዘለቀ ወልደመስቀል	የእድሜ ባለጸጎች ተራድኦ	652974	40404	
23	ዓለምፀሐይ ወርቁ	ዞን 4 ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ	123474	30028	አረ/አካል ጉዳተኛ ክትትል ክፍል
24	ወጋየሁ በለው	አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን	156098	-	ኤክስፐርት
25	ማኬቦ ማራ	ካቶሊክ ቤ/ክ ጨንቻ	06-810182	-	ቡድን መሪ
26	ኃይሉ አበበ	ትግራይ ለምለም ራያ ጡረተኞች ማኅበር	03-402564	288	ምክትል ሊቀመንበር
27	ወልደሃና መዝኚያው	ዞን 5 ወ 9-10-11-18	116516	-	ዋና ፀሐፊ
28	ሓድጉ ገ/ሚካኤል	ዓድዋ ወረዳ አስተዳደር (የአረጋውያን ኮሚቴ ተወካይ)	710275	5	ማሕበራዊ ጉዳይ ዘርፍ
29	አህመድ መሐመድ	ድሬዳዋ ሠ.ማ.ጉ	111273	171	የቡድን መሪ
30	ብርሃኑ ገብሬ	ሐረር ሠ.ማ.ጉ/ አብርሃ ባህታ	662160	210	የማህበራዊ ጠንቅ ባለሙያ
31	ምዑዝ ምሩጽ	ማኅበረ ረዲኤት ትግራይ	412242	20	የፕሮግራም አስተባባሪ
32	ተኽላይ ምርኩዝ	ትግራይ ማ/ዞባ ናዕዴር ዓዴት ወረዳ (የአረጋውያን ኮሚቴ ተወካይ)	-	-	ማህበራዊ አገልግሎት
33	አረጋዊ ገ/ሩፋኤል	ትግራይ ማ/ዞባ ላ/ማይጨው ወረዳ (የአረጋውያን ኮሚቴ ተወካይ)	750249	153	ወረዳ አስተዳዳሪ
34	ተፈራ አይቻ	ሰሜን አሞ ጨንቻ ወረዳ	8	6	የአረጋውያን ኮሚቴ ሰብሳቢ
35	(ካፒቴን) አብርሃም ገዛኸኝ	የኢትዮጵያ አየር/መ ጡረተኞች ማህበር	612222	90391	ምክትል ፕሬዚደንት
36	ጌታቸው ነጋሽ	በመሉ በተቀነባበረ ዘዴ የከተማ ልማት ፕሮጀክት	156375	6889	ሲንየር ኢንስትራክተር
37	ጣሰው ተ/ማሪያም	ቴሌኮሙኒኬሽን ጡረተኞች ማህበር	121212	9607	ዋና ፀሃፊ
38	ዘውዴ በቀለ	ጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር	110752	30742	ዋና ፀሃፊ
39	መሉጌታ ባይህ	የክርስቲያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት	650100	5674	ሲ. ኦፊሰር
40	አክሊሉ ይትባረክ	መድህን ማህበራዊ አገልግሎት ማዕከል	711652	70435	ማህበራዊ አገልግሎት
41	አበራ ቶላ	ሁንዴ	519026	31756	
42	ገና ከዱ	ኦሮሚያ ሠ.ማ.ጉ	517546	21595	መምሪያ ሃላፊ
43	ደምሴ አደፍርሰው	የማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ጡረተኞች ማህበር	553033	34720	ሊቀመንበር
44	ኢየሩሳሌም ምናሴ	የፍቅር ስራ ልጆች የከተማ ልማት	116244	8771	የአረጋውያን ፕሮግራም አስተባባሪ

CCRDA

		ፕሮጀክት			
45	በቀለ ቁምላቸው	ባህር ዳር መድሃኒአለም	180918	191	ፀሐፊ
46	ዝናሽ ታደሰ	ክልል 14 ሠ.ማ.ጉ.	513372	3328	ፀሐፊ
47	ዶ/ር ዳዊት ማሞ	ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ቤ/ክ ምግባረ ሰናይ ማኅበር	114698	55131	
48	አሉላ ተሰማ	ጎንደር ልማት ማኅበር	156428	2348	ዋና ሥራ አስኪያ
49	ንጋት አስፋው	እንረዳዳ አረጋውያን ማህበር	121771	23759	ዳይሬክተር
50	ሰመረ ዘርዑ	የባንክ ባለሙያዎች ጡረተኞች መ/ዕድር	751343	562	ሰብሳቢ
51	ጀምበር ተፈራ	በሙሉ በተቀነባበረ ከተማ ልማት ፕሮጀክት	156375	6889	ፕሮጀክት አስተባባሪ
52	ሰንደቁ ገ/ማርያም	ባህር ዳር መድሃኔ ዓለም የአረጋውያንና የህጻናት ማሳደጊያ			
53	ታደሰ ላፍቴ	መቱ ጡረተኞች ማህበር			
54	ጥላሁን ገብረ ክርስቶስ	ጂማ ጡረተኞች ማህበር	–	571	ከ.ቀ ወ/ጓ/ር
55	አሰፋ ባልሄር	ተሃድሶ መምሪያ			የአረጋውያን ቡድን መ
56	ይበርታ ታደሰ	ሠ.ማ.ጉ. ሚኒስቴር ተሃድሶ ጉዳይ መምሪያ	113026	-	ከፍተኛ ኤክስፐርት
57	ሚ/ር ጆኦፍሬ አዶኖሁዌ	ሔልፐ ኤጅ ኢንተርናሽናል	517748	3384	
58	አምለሰት ቴዎድሮስ	ሔልፐ ኤጅ ኢንተናሽናል	518297	3384	
59	አልማዝ ሚደቅሳ	ሔልፐ ኤጅ ኢንተርናሽናል	518297	3384	
60	ዶ/ር ሚካኤል ደጀኔ	ሔልፐ ኤጅ ኢንተርናሽናል	518297	3384	

CCRDA

አገር አቀፍ የአረጋውያን የጥምረት አውደ ጥናት
የካቲት 19-20/1990
የዓውደ ጥናቱ ፕሮግራም

ሀሙስ የካቲት 19/1990

2፡30	የተሳታፊዎች ምዝገባ
3፡00	የመክፈቻ ንግግር በወ/ሮ መዓዛ መድምም የክልል 14 ሰ/ማ/ጉ/ቢሮ ተወካይ
3፡10	የመግቢያ ንግግር በሄልፕ ኤጅ ኢንተርናሽናል ዳይሬክተር
3፡20	የቅንጅት መሰረታዊ ሃሳቦች ገለጻና ውይይት በፓክት ተወካዮች (አቶ ጸጋዬ ቸርነትና ወ/ሮ ሸዋ ጸሃይ በልሁ)
4፡00	የሻይ እረፍት
4:30	የቅንጅት ዓይነቶች ገለጻና ውይይት በፓክት ተወካዮች
5፡00	የቅንጅት ደረጃዎች በፓክት ተወካዮች
5፡30	በቅንጅት ሊከናወኑ የሚችሉ ስራዎች በፓክት ተወካዮች
6፡30	ምሳ
7፡45	ቅንጅት ሊያጋጥመው የሚችሉ ችግሮች
9፡00	የሻይ እረፍት
9፤30	ቅንጅት በኢትዮጵያ ገለጻና ውይይት በአቶ መሉጌታ ባየህ ክሲአርዲኤ
10፡45	የዕለቱ ፕሮግራም መዝጊያ

ዓርብ የካቲት 20/1990

2፡30	ምዝገባ
3፡00	የኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን - የቅንጅት ሞዴል በአቶ ይበርታ ታደሰ ከተሀድሶ መምሪያ
3፡15	በአረጋውያን ጉዳይ ላይ የሚሰራው ቋሚ ኮሚቴ የስራ ክንውን ሪፖርት በአቶ ደምሴ አቅናው
3፡30	የአረጋውያን ቅንጅት አማራጮችና የወደፊት አቅጣጫ - የቡድን ስራ
4፡45	የሻይ እረፍት
5፡00	የቡድን ስራ ሪፖርት
6፡30	ምሳ
7፡30	የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች የውሳኔ ሃሳቦች
8፡00	1999 ቅንጅት ትብብር በተግባር በአቶ አሰፋ ባልሄር ተሃድሶ መምሪያ
8፤30	የቡድን ስራ በ999 ላይ
9፡15	የሻይ እረፍት
9፡30	አጠቃላይ ግምገማ
4፡45	መዝጊያ

CCRDA